# 1ኛ ሳሙኤል (47)

## ጥናት አንድ 1ኛ ሳሙ 1፡1-28

የጥናት ዓላማ፡- ወደ እግዚአብሄር ለመቅረብና ከጌታ ጋራ በተሻለ ለመኖር በጣርን ቁጥር ጠላታችን ደግሞ ባለው ሃይሉ በመጠቀም ህይወታችንን መራራ ሊያደርግ መሞከሩ እንደማይቀርና እኛም አብዝተን ከእግዚአብሄር ጋራ መጣበቃችንን ከቀጠልን በመጨረሻ ድሉ የእኛ እንደሚሆን ለማወቅና ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- “ይህም በየዓመቱ ይደጋገም ነበር፤ ሐና ወደ እግዚአብሄር ቤት በምትወጣበት ጊዜ ሁሉ፣ እስክታለቅስና መብላት እስኪያቅታት ድረስ ጣውንቷ ታበሳጫት ነበር… ሕልቃና ከሚስቱ ከሐና ጋር ተኛ፣ እግዚአብሄርም አሰባት።” 1ኛ ሳሙ 1፡7፣ 19

1. 1ኛ ሳሙ 1፡1-28 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ1-3ትን በማንበብ ስለ ሕልቃና ቤተሰብ የምታያቸውን እውነቶች ሁሉ በመዘርዘር ተናገር። ሕልቃናና ቤተሰቡ በየዓመቱ እየሄዱ በሚሰግዱበት በሴሎ አገልገሎቱን ይፈጽሙ የነበሩት ካህናቱ እነማን ነበሩ? በዚህ ክፍል ላይ ስንመለከት፤ በእግዚአብሄር ቤተ መቅደስ ውስጥ ያገለግሉ የነበሩትን ሰዎች ስም በመጥቀስ ጸሐፊው መናገር ያስፈለገው ምክንያት በአንተ አመለካከት ምንድነው ብለህ ትገምታለህ?
2. ቁ4-6 ላይ ስንመለከት ሕልቃና ከሁለቱ ሚስቶቹ ይወድ የነበረው ማንን ነበረ? ይህ ሰው ለዚህች ሴት ፍቅሩን ለመግለጽ ይጠቀም የነበረበት መንገድ ምን እንደነበረ ተናገር። ባሏ ምንም ያህል ቢያፈቅራት ከእርሱ ልታገኝ ያልቻለችው ነገር ምን ነበረ? ሕልቃን ሐናን ይህንን ያህል እየወደዳት ውስጧ የሚጠማውን ነገር ለመስጠት አለመቻሉ ምን ያስተምረናል?
3. ቁ9-11ድን ስናነብ ሐና የጸለየችው ጸሎት በህይወቷ የምታልፍበት ሁኔታ አስከፊ መሆኑን በምን መንገድ ይጠቁመናል? ይህች ሴት እግዚአብሄር ማህጸኗን እንዲከፍትና ልጅ እንዲሰጣት ከዚህ በፊት ጸልያ የማታውቅ ይመስልሃል ወይ? ከሆነስ ዛሬ የጸለየችውን ጸሎት በሌላ ቀናት ከጸለየቻቸው ጸሎቶች የሚለየው ምንድነው ብለህ ታምናለህ?
4. ቁ12-16 ላይ ስንመለከት ኤሊ ሐናን ሲመለከት ሊያይ የቻለው ነገር ምኗን እንደነበረና፤ ይህ ደግሞ በመጨረሻ ምን ወደማለት እንዳደረሰው ተናገር። በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ሐና ለካህኑ ልታስረዳ የሞከረችው ነገር ምን ነበረ?
5. ቁ17-20 ላይ ያለውን ክፍል በማንበብ ሐና የጸለየችው ጸሎት የእምነት ጸሎት እንደነበረ የሚጠቁመን ሃሳብ የምናገኘው በየትኛው ክፍል ውስጥ ነው? ሳሙኤል ማለት ትርጉሙ ምን ማለት ነው? ሐና ለልጅ አጥብቃ በጸለየችበት ቁ10ና በቁ20 ማለትም ሳሙኤል በተወለደበት መሃል የነበረው የጊዜ ልዩነት ስንት ሊሆን እንደሚችል አስረዳ። አንተስ የለመንከውን ስትቀበል ከእግዚአብሄር እንደተቀበልከው አስታውሰህ ታመሰግነዋለህ ወይ?
6. ቁ21-23 ስንመለከት ሕልቃና ዓመታዊ ተግባሩን ለመፈጸም ከነቤተሰቡ ወደ ሴሎ ለመሄድ እንደተነሳ እናነባለን። ለፍናና ይህ ጉዞ ከሌላው ጊዜ የተለየ የሚሆነው በምን መንገድ ነው? እንደ ፍናና ዓመት ለዓመት ወይም በኛ ዘመን ደግሞ በየሳምንቱ ሳያቋርጡ ወደ እግዚአብሄር ቤት እየተመላለሱ፣ መስዋዕትና አምልኮ ማቅረባቸውን ሳያቋርጡ፣ ነገር ግን በሌላ ጎኑ የሰዎችን ልብ በሃዘን ለሚወጉና እየተወጉ ላሉት ሰዎች ይህ ክፍል ምን ትምህርት ሊሰጥ ይችላል?
7. ቁ24-28 ለምንድነው ሐና በብዙ ልመናና ጸሎት ያገኘችውን አንድ ልጅ ለእግዚአብሄር ለመስጠት የወሰነችው?
8. ቁ7ትን ወደኋላ መለስ ብለን ስንመለከት የፍናና ሐናን ማበሳጨትና ማስቆጣት እየከፋ የሚሄደው ሐና በህይወትዋ ምን ዓይነት ነገር ለማድረግ ስትነሳ ነው? ሃና ከጌታ ጋራ በመጣበቅ ድልን እንዳገኘች እናያለን፤ የጠላት ሙከራና ደንፋታው ሁሉ ከጌታ ጋራ የሚኖርህን ህይወት ሊቀለብስብህ እንደማይገባ ከሃና ህይወት ተማር።

# ጥናት ሁለት ፩ኛ ሳሙ 2፡1-36

የጥናት ዓላማ፡- እግዚአብሄር በቤቱ ውስጥ ስለራሱ ማንነትና ስለህዝቡ ሲል መልካምን ነገር ሲያደርግ ስናይ፤ በቤተ ክርስትያኒቱ ውስጥ የሚፈጸመውን ማናቸውንም የርኩሰትና የዓመጽ ተግባር የማጽደቁ ምልክት እንደሆነ አድርገን ማየት እንደሌለብን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "አፌ በጠላቶቼ ላይ ተከፈተ፤ በማዳንህ ደስ ይለኛልና...የኤሊ ልጆች ምናምንቴዎች ነበሩ፤ እግዚአብሄርንም አይፈሩም ነበር።" 1ኛ ሳሙ 2፡1 እና 2፡12

1. 1ኛ ሳሙ 2፡1-36 በአንድነት ይነበብ። ከቁ1-11 ባለው ክፍል ላይ ሐናን ምን ስታደርግ ነው የምናያት? ይህ ድርጊቷ ጸሎት ተብሎ መነገሩ ምን ወደሚል መደምደሚያ ይወስደናል? ምዕራፍ አንድንና ምዕራፍ ሁለትን በማንበብ ይህች ሴት በያዕቆብ 5፡13 ላይ የተነገረንን እውነት በህይወቷ ተለማምዳለች ማለት የምንችለው በምን መንገድ ነው?
2. ሐና ደስ እንደተሰኘች በመናገር ደስታዋን ስትገልጽ በቁ1 ላይ እናያታለን። የይህችን ሴት ዝማሬና ጸሎት ስንመለከት ዋነኛው የደስታዋ ምንጭ አድርጋ ያቀረበችው ምንድነው ትላለህ? የሐና ደስታ በትክክለኛው ስፍራ ላይ እንዳረፈ ሊያረጋገጥልን የሚችል ሃሳብ ከእግዚአብሄር ቃል ውስጥ ትዝ የሚልህና ወደ አዕምሮህ የሚመጣው የትኛው ጥቅስ ነው?
3. ቁ12-17ትን እንደገና በአንድነት አንብቡት። የኤሊ ልጆች ክፉና ምናምንቴዎች እንደነበሩ ቁ12 ይነግረናል፤ እነዚህ ልጆች ክፉ ስራቸውን ራሳቸው ሲፈጽሙት አንመለከትም፤ ታዲያ ይህንን ክፉ ስራ የሚያስፈጽሙት በማን በኩል ነበር? የቀድሞው ትርጉም ቁ17 "ሰዎቹም የእግዚአብሄርን ቁርባን ይንቁ ነበር" ይላል። ይህንን ስናነብ የነዚህ የሁለት ሰዎች ተግባር በህዝቡ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ ምን ነበረ? የአገልጋዮች ባህርይና የህዝቡ ህይወት ስላለው ግንኙነት ይህ ክፍል ምን ያስተምረናል?
4. ቁ18-21 በተለይም ቁ18ትን ስናነብ ሳሙኤል እግዚአብሄርን እያገለገለ እንደነበር ይነግረናል። በዚህን ጊዜ ሳሙኤል ገና ብላቴና እንደሆነ፣ የክህነት አገልግሎቱ በኤሊ ልጆች እንደተያዘ እናውቃለን፤ ታዲያ ሳሙኤል በዚያ ዕድሜው ምን ዓይነት አገልግሎት የሚያገለግል ይመስልሃል? እነዚህን ቁጥሮች ስታነብ ሃና ለእግዚአብሄር በሰጠችው በሳሙኤል ምትክ የእግዚአብሄር የተቀበለችው ምን ነገር ታያለህ? ከዚህ አሰራሩ ምን መማር እንችላለን?
5. ቁ22-26 ላይ ልጆቹ በእግዚአብሄር መቅደስ ውስጥና በእግዚአብሄር ህዝብ ላይ ያደርጉ የነበረውን ርኩሰትና አጸያፊ ነገር ሲሰማ ኤሊ የወሰደው እርምጃ ምን ነበረ? እግዚአብሄር በወሰደው እርምጃ እንዳልተስማማ ወረድ ባለው ክፍል ውስጥ እናነባለን። ኤሊ በልጆቹ ላይ መውሰድ የነበረበትና ያልወሰደው እርምጃ ብለህ የምታስበው ነገር ምንድነው?
6. ቁ27-29 ላይ ስናነብ እግዚአብሄር በቤተ መቅደሱ ውስጥ ለሆነው ሁሉ ተጠያቂ ሲያደርግ የምናየው ማንን ነው?
7. ቁ30-36 በቤቱ ውስጥ ለተፈጸመው አጸያፊና ድፍረት የተሞላበት ምግባር የእግዚአብሄር ፍርድ ምን እንደሆነ በአጭሩ ለማስረዳት ሞክር።
8. እግዚአብሄር የሐናን የተዘጋ ማህጸን የመክፈት ተዓምር በሰራበት ወቅት በመቅደሱ ውስጥ ያገለግሉ የነበሩት እነማን ነበሩ? የአገልጋዮቹን ርኩሰትና ዓመጻ አልፎ እግዚአብሄር የህዝቡን ጥማትና ጥያቄ መመለሱ፤ ከዚያም በተጨማሪ ደግሞ ምናምንቴዎች በተባሉት በኤሊ ልጆች ላይ በጊዜው መፍረዱ ለእኛ ምን ሊያስተምረን ይችላል ትላለህ? በእግዚአብሄር ቤት ሲደረግ የምታየው ድፍረት የሞላበት ተግባርና በአንጻሩ ደግሞ እግዚአብሄር ሲሰራ የምታየው ነገር ጥያቄ ሆኖብህ ያውቃል ወይ?

# ጥናት ሶስት 1ኛ ሳሙ 3፡1-21

የጥናት ዓላማ፡- የዔሊ ልጆች እግዚአብሄርንና ቁርባኑን በመናቃቸው ምክንያት እግዚአብሄርን ድምጹን ከህዝቡ እንዳራቀ ሁሉ፤ በአንጻሩ ደግሞ እንደልቡ ሆኖ በትህትናና በአክብሮት የሚያገለግለው ሰው ሲያገኝ እግዚአብሄር ድምጹን ለህዝቡ ለማሰማትና ራሱን ለመግለጥ ወደኋላ እንደማይል ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "በዚያን ዘመን የእግዚአብሄር ቃል ብርቅ ነበረ፤ ራእይም አይታይም ነበር... እግዚአብሄር በሴሎ ይገለጥ ነበር፤ በዚያም በቃሉ አማካይነት ራሱን ለሳሙኤል ገለጠ።" 1ኛ ሳሙ 3፡1 3፡21

1. 1ኛ ሳሙ 3፡1-21 በእንደነት ይነበብ። ቁ1-3ትን በማንበብ ሳሙኤል አገልግሎቱን በጀመረበት ወቅት ስለነበረው መንፈሳዊ ሁኔታ ከነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ልናያቸው የምንችላቸውን ሁኔታዎች ሁሉ አንድ በአንድ በመዘርዘር ተናገር።
2. ቁ4-7 ላይ እግዚአብሄር ደጋግሞ ሳሙኤልን ሲጣራ እናያለን። ሳሙኤል ደጋግሞ የእግዚአብሄርን ድምጽ መለየት ሲሳነውና ወደ ሳሙኤል ሲሄድ ለምንድነው ነገሩ እግዚአብሄርን ቅር ያላሰኘውና ያላስቆጣው? በቁጥር 7 ላይ ሳሙኤል እግዚአብሄርን እንደማያውቅ የተነገረው ነገር፤ በ1ኛ ሳሙ 2፡12 ላይ ስለዔሊ ልጆች በቀደመው ትርጉም "...እግዚአብሄርንም አያውቁም ነበር" ከሚለው አነጋገር ጋራ አንድ ነው ብለህ ታምናለህ ወይ? አስረዳ።
3. ሳሙኤልን እግዚአብሄር በአጠቃላይ ስንት ጊዜ ነው የጠራው? እግዚአብሄር ሳሙኤልን እየጠራው እንደሆነ ዔሊ የተገነዘበው በስንተኛው ጊዜ ነው? ይህ ሊቀ ካህን በእግዚአብሄር አገልግሎትና በእግዚአብሄር ቤት ይህንን ያህል ረጅም ጊዜ የቆየ ሰው ለምን ይመስልሃል በመጀመሪያው ጥሪ እግዚአብሄር እየጠራው እንደነበር መለየት ያልቻለው?
4. በቁ9-10 ላይ ስናነብ ዔሊ ሳሙኤልን የጠራው እግዚአብሄር እንደሆን በተረዳ ጊዜ ለብላቴናው የለገሰው ምክር ምን የሚል ነበረ? በሌሎቹ ጥሪዎች ውስጥ የማናየውና በቁ10 ላይ በምናገኘው ጥሪ አራተኛ ጥሪ ውስጥ የምናነበው አንድ አዲስ ነገር ምን ታያለህ? ሳሙኤል ገና ብላቴናም ቢሆን በመንፈሳዊ ህይወቱ ምናልባትም ከዔሊ በተሻለ ሁኔታ የሚገኝ፣ ወደፊትም ደግሞ ክህነቱን ተረካቢ እርሱ መሆኑ አውቆት ሳለ፤ ምሪትን ከዔሊ ተቀብሎ በተግባር ላይ ለማዋል መወሰኑ ምን ሊያስተምረን ይችላል?
5. ሳሙኤል በመጨረሻ እየጠራው ያለው እግዚአብሄር እንደነበረ ከተነገረው በኋላ በመኝታው ሆኖ ያስብ የነበረውንና ሊሰማው ስለሚችለው ስሜት የሚመስልህን ተናገር። በቁ10 ላይ ሳሙኤል እግዚአብሄር ሲጠራው "ባሪያህ ይሰማልና ተናገር" የተናገረው አነጋገርን ስንመለከት፤ "ባሪያህ" የሚለው አባባል በዚህ ዓውደ ምንባብ ውስጥ ያዘለው ትርጉም ምንድነው ትላለህ?
6. ቁ11-14 ላይ ስንመለከት ለመጀመሪያ ጊዜ ሳሙኤል ከእግዚአብሄር የመስማት እድል ገጥሞት እናያለን። እግዚአብሄር ለመጀመሪያ ጊዜ ለሳሙኤል የተናገረው መልዕክት በይዘታው ምን ይመስላል? ሳሙኤል እንደ ባሪያ እግዚአብሄር እንዲናገረውና እርሱም ያለውን እንደሚያደርግ ተናግሯል፤ ታዲያ ይህ ከእግዚአብሄር የተቀበለው የመጀመሪያ መልዕክቱ ለማስተላለፍ ከባድ የሚሆነው ለምንድነው? እግዚአብሄር በዔሊ ቤት ላይ የተናገረውን ለመፈጸም የምሩን መሆኑን በምን ማየት ይቻላል?
7. ቁ15-16 ላይ "ሳሙኤል እስኪነጋ ድረስ ተኛ" ሳሙኤል መልዕክቱን ከተቀበለ በኋላ እንቅልፍ የወሰደው ይመስልሃል ወይ? እስከሚነጋ ድረስ በአዕምሮው ይመላለስ የነበረው ሃሳብ ምን ሊሆን እንደሚችል ተናገር። በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ሳሙኤል በቤተ መቅደሱ ውስጥ ሲያገለግል ይሰራ ከነበራቸው ስራዎች አንዱን እናያለን፤ በዚህ ክፍል የምናየው ይህ የሳሙኤል አገልግሎት ምን ነበረ?
8. ቁ17-21 እንደገና በአንድነት አንብቡትና፤ በቁ1 እስራኤል የነበረበትን ሁኔታና በዚህ ክፍል ሳሙኤል ከመጣ በኋላ ደግሞ ግልጽ ሆኖ የሚታየው አንድ ልዩነት ምን እንደሆነ አስረዳ። እግዚአብሄርን የሚንቁ አገልጋዮች በሞሉበት ቤት ክርስትያንና፤ በእርሱ ፍርሃት የሚያገለግሉ ሰዎች በሞሉበት ቤ/ክ የእግዚአብሄር አሰራር ልዩነት አለው ብለህ ታምናለህ ወይ? እግዚአብሄር በህይወታችን ድምጹን ከማሰማትና ራሱን ከመግለጥ እንዳይከለከል ካስፈለገ በእግዚአብሄር ፍርሃትና በቅድስና መመላለስ አማራጭ የሌለው ነገር ነው።

# ጥናት አራት ፩ኛ ሳሙ 4፡1-22

የጥናት ዓላማ፡- የታቦቱ ወደ ጦር ሜዳ መምጣት ለእስራኤል የደስታ ጩኸትን እንጂ የድል ምንጭ እንዳልሆነላቸው ሁሉ፤ እግዚአብሄር ከእኛ ጋራ እንዲወጣና በጠላታችን ፊት ድል እንዲሰጠን ካስፈለገ፤ የሚያስፈልገው ጩኸትና ጫጫታ ሳይሆን ራስን አዋርዶ በትህትና የአምላክን ፊት መፈለግና በንስሃ ሃጥያትን መናዘዝ እንደሆነ ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- “የእግዚአብሄር የኪዳኑ ታቦት ወደ ሰፈር በገባ ጊዜ ምድሪቱ እስክትናወጥ ድረስ እስራኤላውያን ሁሉ ታላቅ የደስታ ጩኸት አሰሙ...የእግዚአብሄር ታቦት ተማረከ ሁለቱም የዔሊ ልጆች አፍኒንና ፊንሃስ ተገደሉ።” ፩ሳሙ 4፡5፣ 11

1. ፩ኛ ሳሙ 4፡1-22 በእንደነት ይነበብ። በቁ1 ላይ “የሳሙኤል ቃል” በመባል የተነገረው ሳሙኤል ራሱ ለህዝቡ ሊናገረው ከራሱ ያመነጨው ሃሳብ ነበር ወይስ ከፍሉ የሚናገረው ስለየትኛው ቃል ነው? ቁ1-2ትን ብቻ በማንበብ በእስራኤልና በፍልስጤም መሃል የተካሄደው ነገር ምን እንደነበረና ውጤቱንም ጭምር በዝርዝር ተናገር።
2. እስራኤላውያን ለመሸነፋቸው ምክንያት አድርገው የተቀበሉት ነገር ምን ነበረ? በቁ3 ላይ የተሰነዘረው ጥያቄ የቀረበው ለማን ነበረ? በጦርነቱ ለደረሰባቸው ሽንፈት ተጠያቂ ወይም ምክንያት አድርገው ያመኑት እግዚአብሄርን ከሆነ፤ ይህ ጥያቄ መቅረብ የነበረበት ለማን ነበረ ብለህ ታምናለህ? ለራሳቸው ጥያቄ ራሳቸው መልስ ሲሰጡ ይታያል፤ ችግራቸው መፍትሄ አድርገው የወሰዱት ነገር ምን ነበረ?
3. ቁ4ትን ስናነብ የእግዚአብሄር ታቦት ሲመጣ ከታቦቱ ጋራ አብረው የመጡት ሰዎች እነማን ናቸው? ስለነዚ ሰዎች ከቀደሙት ምዕራፎች ውስጥ የምናውቃቸው እውነቶች ምን ታስታውሳለህ? እነዚህ አፍኒንና ፊንሃስ ታቦቱን ተሸክመው ሲመጡ ሲያዩ ህዝቡ ያደረጉት ነገር ቁ5ትን ስንመለከት ምን ነበረ? በአንተ አመለካከት ህዝቡ ካሳየው የደስታ ስሜት ይልቅ ሊያደርግ የሚገባው ምን ነበረ ብለህ ታምናለህ? ለምን?
4. ቁ5-9 ስናይ እስራኤል በታቦቱ መምጣት ይህን ያህል ደስታ የተሰማቸው ለምንድነው? ፍልስጤማውያንስ በታቦቱ መምጣት ይህንን ያህል ፍርሃት ያደረባቸው ለምን ይመስልሃል? በኢያሱ 6፡12ትና በሌሎችም በተለያዩ ጦርነቶች ላይ የእግዚአብሄር ታቦት ከህዝቡ ጋራ በጦር ሜዳ ተሰልፎ ድል ሲያደርግ ይታያል፤ ታዲያ በዚህ ጦርነት ላይ በታቦቱ ድል ያልተገኘበት ምክንያት ለምንድነው ትላለህ?
5. ቁ10-11ድን ስናነብ ፍልስጤማውያን ድል ሲያደርጉ ይታያል። የእስራኤልን ተሸናፊነት ጉልህ አድርገው የሚያሳዩ አራት ነገሮች በነዚህ ሁለት ቁጥሮች ውስጥ ያሉትን በመዘርዘር ተናገር።
6. ቁ12-18 ውስጥ ሊቀ ካህኑ ኤሊ በጭንቀት ውስጥ እንደነበረ ይታያል፤ ዔሊን ያስጨንቅ የነበረው ዋነኛው ነገር ምን ነበረ? ይህ ሰው እግዚአብሄር እንደሌሎች አማልክት ለራሱ መዋጋት የማይችል አምላክ አድርጎ ስላየው ነው ወይስ ለእግዚአብሄር ታቦት የተጨነቀበት ምክንያት ለምንድነው ብለህ ታምናለህ?
7. በቁ19-22 ላይ የካህኑ የፊንሃስ ሚስት ከጦር ሜዳ በመጣው ዜና ምክንያት ያለፈችበትን ሁኔታ ይነግረናል። ይህች ሴት በቁ22 ላይ “የእግዚአብሄር ታቦት ተማርኳልና ክብር ከእስራኤል ተለይቷል” ብላ ስትናገር እናያለን። በዚህ አነጋገሯ ትስማማለህ ወይ? ለምን?
8. ፩ኛ ሳሙ 4፡5 እና ቁ11ድን ስናነብ ታቦቱን ወደ ጦር ሜዳ እንዳስመጡት፤ በታቦቱም መምጣት ታላቅ ደስታና ጩኸት ህዝቡ እነዳሰሙ እናነባለን። የእግዚአብሄር ታቦት በመሃላቸው እያለ፤ ህዝቡም የደስታ ጩኸት እያሰሙ ባሉበት ሁኔታ ውስጥ በጠላቶቻቸው ድል መመታታቸው ምን ሊያስተምረን ይችላል? ታቦት የተሰጣቸው የእግዚአብሄር በመሃላቸው የመገኘት ምልክት እንጂ ራሱ ታቦቱ እግዚአብሄር እንደሆነ አድርገው መቁጠራቸው ትልቅ ስህተት ነበረ፤ ስለዚህ እኛም እርሱን ለማምለክ እንዲረዱ የተሰጡን ማናቸውንም ነገሮች በእግዚአብሄር ምትክ አድርገን እንዳናያቸው ልትጠነቀቅ ይገባናል።

# ጥናት አምስት ፩ኛ ሳሙ 5፡1-6፡21

የጥናት ዓላማ፡- እግዚአብሄር የሰዎችን ዓይን ከፍቶ የወንጌልን እውነት እንዲያዩ ካላደረገ በስተቀረ፤ ብዙ የተዓምራት አይነቶችን በዙሪያችን ሲከናወኑ ብናይ ወደ ደህንነት ሊያደርሰን ስለማይችል፤ መንፈስ ቅዱስ የሰዎችን ዐይን ከፍቶ እውነቱን ማየት እንዲችሉ መጸለይ ቅድሚያ ልንሰጠው የሚገባን ነገር እንደሆነ ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- “ወደ ቤትሳሚስ አቅጣጫ ወደ ገዛ አገሩ የሚሄድ ከሆነ፣ ይህን ታላቅ መከራ ያመጣብን እግዚአብሄር ነው...የፍልስጤም ገዦችም እስከ ቤትሳሚስ ድንበር ተከተሏቸው።” 1 ሳሙ 6፡9-12

1. 1ኛ ሳሙ 5፡1-6፡21 በእንደነት ይነበብ። ቁ1-5 በጦርነት የተማረከው የእግዚአብሄር ታቦት ራሱን በምን ዓይነት ስፍራ ነው ያገኘው? ታቦቱ ቀድሞ ከነበረበት ሁኔታ ዛሬ የሚገኝበት ሁኔታ ልዩ የሚያደርገው ነገር ምንድነው። የፍልስጤማውያን አምላክ  በእስራኤል አምላክ በእግዚአብሄር ታቦት ፊት በተደጋጋሚ ወድቆ ሲያገኙት፤ የፍልስጤማውያንና የዳጎን ካህናት ምላሽ ምን ነበረ?
2. የእግዚአብሄር ታቦት በአምላካቸው ላይ ያደረገውን ተአምራት በማየት ለመመለስ እንቢ ሲሉ ማድረግ የጀመረው ነገር ምንድነው? ብዙ የጦር ሃይል ተሰልፎበት ከነበረው ከእስራኤል ጋራ ካካሄዱት ጦርነት ይልቅ የፍልስጤም ህዝብ የተረታው መቼ ነው? የእግዚአብሄር ታቦት በምርኮ አገር ሆኖ ለብቻው የጠላትን ሰፈር ሲያንቀጠቅጥ፤ የእስራኤል ሽማግሌዎችና ህዝቡ ያስቡ የነበረው ነገር ምን ይመስልሃል? አንዳንድ ጊዜ ያለእኛ እግዚአብሄር እጁ የታሰረ ለሚመስለን ሰዎች፤ እርሱ መስራት ከፈለገ የሰው እርዳታ እንደማያስፈልገው ከዚህ ክፍል ልንረዳ ይገባናል።
3. እግዚአብሄር በምዕራፍ አምስት ውስጥ ያደረጋቸውን ነገሮች ሁሉ በማየት የፍልስጤም ህዝብ በ6፡2 ላይ “የእግዚአብሄርን ታቦት ምን እናድርገው?” በማለት ሲጠይቁ እናያለን። ለዚህ ጥያቄአቸው ምላሽ ሆኖ የታያቸው ነገር ምን ነበረ? ለዚህ ጥያቄአቸው ምላሽ ሊሆን የሚገባው ነገር ምን ነበረ ብለህ ታምናለህ? አንዳንዴ እኛ በተለያየ መንገድ ሲናገረን ከመታዘዝ ይልቅ፤ ስለዚያ ነገር ከእግዚአብሄር ላለመስማት የራሳችንን መንገድ በመከተል ድምጹን ከእኛ ለማራቅ ስንሞክር እንዳንገኝ ልንጠነቀቅ ይገባናል።
4. ቁ3-6 ላይ ስናነብ እነዚህ የፍልስጤም ካህናትና ጠንቋዮች ስለሁኔታው የተረዱት አንድ እውነት ምን ነበረ? በቁ5 እና 6 ላይ እነዚህ የፍልስጤም ካህናትና ጠንቋዮች ስለእግዚአብሄር የሚናገሯቸው እውነት የሆኑ ነገሮች የምታያቸውን ተናገር። እግዚአብሄር በእርሱ ቤት ሆነው እርሱን ከሚያቃልሉት ካህናቱ አፍኒንና ፊንሃስ እነዚህ የተሻለ አምለካከት እንዳላቸው ይታይሃል ወይ?
5. ዘሁልቁ 7፡9 ላይ እግዚአብሄር የሰጠውን ትዕዛዝ ስንመለከት፤ በቁ8 ላይ የፍልስጤም ካህናትና ጠንቋዮቹ የሰጡት ምክር የተሳሳተና በእግዚአብሄር የሚያስቀስፍ የሚሆነው ለምንድነው? የእግዚአብሄርን ታቦት እነርሱ በነገሯቸው መንገድ እንዳጓጓዙትና እግዚአብሄርም ይህንን ስላደረጉ ሲቀጣቸው አናይም፤ ይህ የሆነው ለምን ይመስልሃል? ከዚህ ሁኔታ ምን መማር እንችላለን?
6. ቁ13-18ትን ስናነብ በምርኮ አገር ለሰባት ወር የሰነበተው የእግዚአብሄር ታቦት ተመልሶ በመምጣቱ የቤትሳሚስ ሰዎች የትሰማቸው ስሜት ምን ነበረ? ህዝቡ ለሚቃጠል መስዋዕትነት የተጠቀሙባቸውን ነገሮች ከየት የመጡ ነበሩ? ታቦቱ ተጭኖበት የመጣው ሰረገላ ለወደፊት ታቦቱን ለማጓጓዣ እንዲገለገሉበት ለምን አላስቀሩትም?
7. በቁ19-20 ላይ እግዚአብሄር ወደ ታቦቱ ውስጥ በመመልከታቸው የቤትሳሚስ ሰዎች ጥቂቶቹን በሞት እንደቀጣ እናያለን። በአንተ አመለካከት የታቦቱን የውስጡን ክፍል ለማየት የተነሳሱበት ምክንያት ለምንድነው ብለህ ታስባለህ? የቤትሳሚስ ሰዎች እግዚአብሄር ከወሰደው እርምጃ በውስጣቸው የፈጠረባቸው ስሜትና አንድ ውስጣቸው የቀረ እውነት ምን ነበረ?
8. በአምላካቸው በዳጎን ላይ እንዲሁም በየከተማቸው ላይ እግዚአብሄር ያደረገውን አይተው፤ በተጨማሪ ላሞቹ የሚሄዱበት አቅጣጫ የሆነው ሁሉ በእግዚአብሄር መሆኑን አረጋግጠው ሳሉ፤ ነገር ግን ወደ እግዚአብሄርን ለማምለክና እርሱን ለመምረጥ አለመወሰናቸው ምን ያስተምረናል? ሰዎች በራሳቸው እውነትን ማየት እንደማይችሉና መንፈስ ቅዱስ ራሱ ዓይኖቻቸውን እንዲከፍትላቸው መጸለይ እንደሚኖርብን ከዚህ ክፍል ግልጽ የሆነ ትምህርት መቅሰም እንችላለን።

# ጥናት ስድስት 1ኛ ሳሙ 7፡1-17

የጥናት ዓላማ፡- እስራኤል በመከራቸው ጊዜ የመጀመሪያ መፍትሄ እግዚአብሄርን እንዳደረጉ፤ እኛም በህይወታችን በመከራ ተከበን ራሳችንን ስናገኘው የመጀመሪያና ብቸኛ መልስ አድርገን ለመፍትሄ የምንሮጠው ወደ እግዚአብሄር ሊሆን እንደሚገባ ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "…ይህን ሲሰሙ ፍልስጤማውያንን ፈሩ፤ ሳሙኤልንም አምላካችን እግዚአብሄር ከፍልስጤማውያን እጅ ያድነን ዘንድ ስለእኛ ወደ እርሱ መጸለይህን አታቋርጥ አሉት።" 1ሳሙ 7፡8

1. 1ኛ ሳሙ 7፡1-17 በአንደነት ይነበብ። ቁ2-3 በማንበብ ሳሙኤል ለተናገረውና ሊያደርግ ላሰበው ነገር መንገድ የከፈተለት ወይም ያቀለለለት ብለህ የምታየው ነገር ምንድነው? እነዚህን ቁጥሮች ትኩረት ሰጥተን በምንመለከትበት ጊዜ የንስሃ ሁለት ገጽታዎች ጉልህ ሆነው እንመለከታለን፤ እነዚህ ሁለቱ ነገሮች ምንና ምን እንደሆኑ አስረዳ።
2. በቁ 3 ላይ ሳሙኤል ህዝቡን እውነተኛና ከልብ የሆነ ንስሃ እንዲገባ ሲጠይቅ፤ ከእግዚአብሄር ጋራ ህይወታቸውን በማስተካከላቸው ከሚያገኙት በረከት መሃል አንዱን ጠቅሷል፤ ይህ ሳሙኤል የጠቀሰው ነገር ምን ነበረ? አንተስ ዛሬ እግዚአብሄር በህይወትህ ጣልቃ እንዲገባልህ የምትፈልገው በየትኛው ነገርህ ውስጥ ነው?
3. በቁ2-6 ላይ በእስራኤላውያን ህይወት የተካሄዱት ነገሮች ሁሉ፤ በቁ7-11 ለተካሄዱት ነገሮች አስተዋጽዖ አድርገዋል ብለህ ታምናለህ ወይ? አዎን አድርገዋል ካልክ ደግሞ በምን መንገድ አስተዋጽዖ እንዳደረጉ አስረዳ።
4. በቁ2-6 ላይ ህዝቡ እግዚአብሄር የሚፈልግባቸውን ትክክለኛ ነገር ሲያደርጉ ነው የምንመለከተው። ቁ7 ላይ ስንመለከት ደግሞ ጠላቶቻቸው ሊወጓቸው እንደመጡ እናያለን። እስራኤላውያን እግዚአብሄርን በመፈለግና በጽድቅ ህይወታቸውን በመምራት ላይ እያሉ ጠላት ደግሞ እነርሱን ለማጥቃት መነሳቱን ስንመለከት፣ ከዚህ መማር የምንችለው እውነት ምንድነው? ትክክለኛውንና እንደ እግዚአብሄር ፈቃድ የሆነውን ነገር ለማድረግ ስትሞክር ጦርነት የበዛብህን ጊዜ ታስታውሳለህ ወይ?
5. በቁ7-11 ውስጥ ስንመለከት እስራኤል ከሃያ አመታት በላይ በጠላቶቻቸው ሲረገጡና ድል ሲመቱ ቆይተው አሁን ይህ ሁኔታ እንዲቀየር የሆነው በምን ምክንያት ነው ብለህ ታምናለህ? በ1ኛ ሳሙ 7፡7-11 ላይ ሳሙኤል ሲጠቀምበት የምንመለከተው የጦርነት ስልት በ1ኛ ሳሙ 4፡1-4 የእስራኤል አለቆች ሲጠቀሙበት ከምናነበው የጦር ሥልት የሚለይው በምን መንገድ ነው?
6. ቁ10ን ስናነብ ፍልስጤማውያን እስራኤላውያንን ለመውጋት የቀረቡት በምን ዓይነት ጊዜ ነበረ? ይህንን ስናነብ ከዚህ ሁኔታ ለህይወታችን ልንማረው የምንችለው አንድ እውነት ምንድነው?
7. አቤንኤዘር ወይም "እግዚአብሄር እስከ አሁን ድረስ ረድቶናል" የሚለው የሳሙኤል አነጋገር በጥልቀት ለተመለከተው ሰው፤ እስራኤል ዛሬ ድል ከማድረጋቸው አልፈው ስለወደፊቱ ደግሞ ሊረዱት የሚገባቸው ቢያንስ ሁለት እውነቶችን በውስጡ አዝሏል። እነዚህ ሁለት ሃሳቦች ምንና ምን እንደሆኑ ተናገር።
8. በቁ7-8 ላይ መለስ ብለን ስንመለከት የእስራኤል ህዝብ ፍልስጤማውያንን በፈሩ ጊዜ የወሰዱት የመጀመሪያ እርምጃ ምን ነበረ? አንተስ በመከራ ተከበህ ራስህን ስታገኘው በመጀመሪያ ለማድረግ የምትሞክረው ነገር ምንድነው? በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ገብተን ራሳችንን በምናገኝበት ወቅት ልንወስደው የሚገባን የመጀመሪያ እርምጃችን የአምላካችንን የእግዚአብሄርን ስም መጥራት ሊሆን ይገባል።

# <u>ጥናት ሰባት ፲ኛ ሳሙ 8፡1-22</u>

የጥናት ዓላማ፡- ባላመኑት ሰዎች የምንቀናባቸው ማናቸውም ነገሮች ወደ ህይወታችን ስናስተናግዳቸው ህይወታችን የሚያራቁቱና የሚያጎሳቁሉ ሲሆኑ፤ እግዚአብሄር ግን ለእኛ ከመስጠትና ከመጠንቀቅ ሌላ ከእኛ የሚፈልገው ምንም ነገር እንደሌለ ለመማር።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "በላያችሁ የሚነግሰው ንጉስ የሚያደርግባችሁ ይህ ነው፤ ወንዶች ልጆቻችሁን ወስዶ ሰረገለኞችና ፈረሰኞች ያደርጋቸዋል፤ በሰረገሎቹም ፊት ይሮጣሉ።" ፲ኛ ሳሙ 8፡11

1. ፲ኛ ሳሙ 8፡1-22 በእንደነት ይነበብ። በቁ1-3 ውስጥ ያለውን ስትመለከት ሳሙኤልና ካህኑ ኤሊ የሚመሳሰሉበት ምን ነገርን ትመለከታለህ? እነዚህን ሶስት ቁጥሮች ስናነብ የሳሙኤል ልጆች ሹመታቸውን በምን ሁኔታ ነበረ የተጠቀሙበት?
2. ለእስራኤል ሽማግሌዎች ንጉስ እንዲያነግሥላቸው ሳሙኤልን ለመጠየቅ ምክንያት አድርገው ያቀረቧቸው ሁለት ነገሮች ምንና ምን ነበሩ? እነዚህ ሽማግሌዎች ያቀረቧቸው ምክንያቶች እውነተኛ ምክንያቶች መሆናቸውን ለማረጋገጥ ከምንባቡ ውስጥ ሃሳቡን የሚደግፉ ክፍሎች የት እንደሚገኙ ተናገር።
3. በቁ5 ላይ ስንመለከት እስራኤላውያን ከሌሎቹ በአካባቢያቸው ከነበሩት ህዝቦች ሁሉ የተለየ የሚያደርጋቸው አንድ ነገር ምን ነበረ? በዚህ ቁጥር ላይ ይህ እስራኤላውያንን ከሌሎች ልዩ ያደረጋቸውን ሁኔታ እንዳልወደዱትና እንዳልተስማማቸው ግልጽ የሚያደርግልን ሃሳብ የትኛው ነው?
4. በዚህ ምንባብ ውስጥ ስንመለከት፤ የሳሙኤልን ልብ በጣም ያሳዘነው ነገር ምን ነበረ? እነዚህ የእስራኤል ሽማግሌዎች በወሰዱት እርምጃና በውሳኔአቸው ባዘነበት ሰዓት ሳሙኤል ያደረገው የመጀመሪያ ነገር ምን ነበረ? እርሱ በዚህ ሥፍራ ከወሰደው እርምጃ ሌላ አስቀድሞ ሊያደርግ የሚችለው ምን ነገር ሊኖር እንደሚችል የምትገምተውን ተናገር። አንተስ ሰዎች ልብህን የሚሰብርና የሚያሳዝንህን ነገር ሲያደርጉ የመጀመሪያ እርምጃህ ምን ይሆን?
5. ቁ7 ላይ ስንመለከት ህዝቡ ንጉስ እንዲያነግሥላቸው የጠየቁትን ጥያቄ እግዚአብሄር እንደንቀት እንደተመለከተው እናነባለን። ለምን ይመስልሃል ይህ ጥያቄ በእግዚአብሄር አመለካከት ከንቀት የተቆጠረው? ጥቂት ቁጥሮች ብቻ ወደኋላ ሄደን ፲ኛ ሳሙ 7፡10-13ን ስናነብ ንጉሳቸው የነበረው እግዚአብሄር ያደረገላቸውን ድንቅ ነገር አይተው፤ በጥቂት ጊዜ ውስጥ ዛሬ ወደዚህ ዓይነት ጥያቄ መድረሳቸው ስለሰው ልብ ምን ሊያስተምረን ይችላል ትላለህ?
6. በቁ20 ላይ "ንጉሥ ያለን ሕዝቦች እንሆናለን" ከሚለው አነጋገር በመነሳት እነዚህ ህዝቦች አንድ የተሳሳተ አመለካከት እንዳላቸው ይጠቁመናል፤ ይህ የተሳሳተ አመለካከታቸው ምንድነው? የዚህ ዓይነት የተሳሳተ አመለከከት ሊኖራቸው የቻለበት ምክንያት ለምን ይመስልሃል?
7. ቁ11-18ትን በምናነብበት ጊዜ አህዛብን ለመምሰል የጠየቁት ንጉሥ በማድረግ የሚታወቀውና በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ቢያንስ ለ5 ጊዜ ያህል ተደጋግሞ የተጠቀሰው አንድ ቃል ምንድነው? በተቃራኒው ደግሞ ቀድሞ ይገዛቸው የነበረው እግዚአብሄርስ የሚታወቅበት አንድ ነገር ምንድነው ብትባል ምን ትላለህ? አንተስ ሌሎች ያላቸውና የሚኖሩት ኑሮ አስቀንቶህ ያውቃል ወይ? በሌሎች የምንቀናባቸው ነገሮች በህይወታችን ያለውን ነገር የሚወስዱና የሚያጎሳቁሉን እንደሆኑና፤ እግዚአብሄር ግን ሁልጊዜ ለእኛ ለመስጠትና ከእስራታችን ለመፍታት ያለ መሆኑን እናስታውስ።

# <u>ጥናት ስምንት ፲ኛ ሳሙ 9፡1-27</u>

የጥናት ዓላማ፡- እግዚአብሄር አምላክ ትልቅ የሆነን ነገር ለማከናወን ሲፈልግ አንዳንድ ጊዜ መለኮታዊ የሆነና እኛ ይሰራብታል ብለን በምንጠብቀው መንገድ ሳይሆን ሁኔታዎችን በማቀነባበር የራሱን ሃሳብ ሊያከናውንና ሊሰራ እንደሚችል ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- “ከአገልጋዮቹ መካከል አንዱን ይዘህ ሂድና አህዮቹን ፈልግ አለው” ፲ኛ ሳሙ 9፡3 “ነገ በዚህ ጊዜ ከብንያም ምድር አንድ ሰው ወደ አንተ እልካለሁ፤ በህዝቤ በእስራኤል ላይ መሪ እንዲሆን ቀባው።” ፲ኛ ሳሙ 9፡16

1. ፲ኛ ሳሙ 9፡1-27 በእንደነት ይነበብ። በቁ1-2 ስለሳኦል የተነገሩትን ነገሮች ዘርዝር። በነዚህ ሁለት ቁጥሮች ውስጥ ስለ ሳዖል ከምናነባቸው ነገሮች መሃል ከእግዚአብሄር ጋራ ስለነበረው ግንኙነት ምን የሚነግረን ነገር አለ?
2. በቁ6 ላይ ስለ የሳሙኤልን ማንነት ለመግለጥ የተጠቀመባቸውን አነጋገሮች ተናገር። እነዚህ ሰዎች ለምንድነው ወደ ሳሙኤል መሄድ ያስፈለጋቸው? አንተስ፤ ሰዎች ግራ ሲጋቡና ትክክለኛውን መንገድ የሚጠቁማቸው ሰው ሲፈልጉ ልባቸው ወዳንተ ለመምጣት እንዲችሉ የሚያደርጋቸው ነገር አለህ ወይ?
3. የሳሙኤልን ትክክለኛ ማነነትና መንፈሳዊ ብቃቱን ሁሉ እያወቁ በቁ6-10 ላይ ስናነብ ግን የሳዖልና የአገልጋዩ ውይይት ወይም ልባቸው በምን ላይ ነበረ ማለት እንችላለን? ከዚህ ሁኔታ ስንመለከት የሳዖልና የአገልጋዩ ልብ ስለሚገኝበት መንፈሳዊ ሁኔት ምን መናገር እንችላለን?
4. ምንም እንኳን ሳዖል እግዚአብሄርን የመፈለግና መንፈሳዊ ጥማት ባናይበትም፤ ቁ15-16 ላይ ከምንመለከተው ነገር፤ እግዚአብሄር አምላክ ሳዖልን አስመልክቶ እንደሚያውቅ የምንረዳው ነገር ምንድነው? እግዚአብሄርን ከሚፈሩትና ከሚወዱት ሰዎች አልፎ እግዚአብሄር ልባቸው በእርሱ ላይ ያልሆኑትን ሰዎችም ጭምር እንቅስቃሴ ማወቁ የሚያስተምረን ነገር ምንድነው?
5. ቁ15-16ትን ስናነብ አመጸኛ ሆኖ እግዚአብሄር ንጉሳችን አይሆንም ብለው ንጉስ እንዲነግስላቸው የጠየቁትን ሰዎች በዚህ ክፍል ውስጥ ምን በማለት ነው የሚጠራቸው? ይህንንስ አባባል በነዚሁ ሁለት ቁጥሮች ውስጥ ብቻ ስንት ጊዜ ሲጠቀምበት እንመለከታለን? እግዚአብሄር እነዚህን እርሱ ንጉሳችን አይሆንም ብለው የናቁትን ሰዎች ምን ለማድረግ ዕቅድ ሲያወጣ ነው የምናየው?
6. ቁ21ድን ስንመለከት ሳዖል ህይወቱን በትህትና ሲጀምር ይታያል፤ ሆኖም ሳዖል በዚህ ትህትናው እንዳልቀጠለበት እናውቃለን። ታዲያ እግዚአብሄር በትህትና ጀምሮ በትህትና እንደሚጨርስ አላወቀም ነበረ ወይ? ይህንንስ የሚያውቅ ከሆነ ለህዝቡ ለምን የዚህ ዓይነት ሰው ይሰጣቸዋል?
7. ቁ22-27 ላይ ስናነብ ሳዖል ከሌሎች የተለየ ሥጋ፣ ከሌሎች የተለየ ወንበር፣ ልዩ ሥፍራና ከነብይ ጋራ ተቀምጦ የሚበላበት ሁኔታ እንደተዘጋጀለት እናነባለን። ይህ የጠፉ አህዮችን ፍለጋ የወጣ ሰው በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ራሱን ሲያገኘው ሊሰማው ስለሚችለው ስሜት ተወያዩበት።
8. ቁ3-5 ላይ ተመልሰን ስንመለከት እግዚአብሄር ንጉስን የሚያህል ነገር ወደ ዙፋን ለማምጣት ሲጠቀም የምናየው መንገድ ምንድነው?። ጥቃቅን በሚመስሉ እለታዊ ተግባሮችህ ውስጥ እግዚአብሄር ፈቃዱን ሊፈጽም እንደሚችል አትዘንጋ። ሁልጊዜ እግዚአብሄር ትልልቅ በሆኑና በሰዎች ዓይን ሥፍራ በሚሰጣቸው አይነት ሁኔታዎች ሳይሆን፤ ሰው ሥፍራ በማይሰጣቸው ሁኔታዎችም ውስጥ ፈቃዱን ሊፈጽም እንደሚችል መዘንጋት አይኖርብንም።

# ጥናት ዘጠኝ ነኛ ሳሙ ነ0፡ነ-27

የጥናት ዓላማ፡- ሳሙኤል በሳዖል ህይወት ብዙ አስገራሚ ነገሮችን እንደተናገረና እንደተፈጸሙ ሁሉ፤ ሰዎች ብዙ ነገር በህይወታችን አስተዋጾዖ ሊያደርጉ ይችላሉ፤ ሆኖም ለሰዎች የልብ ለውጥን ሊሰጥ የሚችለው እግዚአብሄር አምላክ ብቻ እንደሆነ አስረግጠን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- “ሳዖል ከሳሙኤል ተለይቶ ለመሄድ ፊቱን በመለሰ ጊዜ፣ እግዚአብሄር የሳዖልን ልብ ለወጠው፤ ምልክቱም ሁሉ በዚያ ዕለት ተፈጸመ።” ነ ሳሙ ነ0፡9

1. ነኛ ሳሙ ነ0፡ነ-27 በአንድነት ይነበብ። ሳሙኤል በቁነ ላይ ሲያደርግ የምናነባቸው ሶስት ነገሮች ምን ምንድናቸው? በዚህ ክፍል ውስጥ የነብዩ ሳሙኤል ሳዖልን መሳም ምንን የሚያመለክት ይመስልሃል? “በርስቱ ላይ ገዥ ትሆን ዘንድ” በማለት ለሳዖል የተነገረው ነገር ምንን ሊያስገነዝበው ፈልጎ ነው ትላለህ?
2. ለሳዖል በእርግጥ እግዚአብሄር እንደተናገረውና በልቡ ምንም ዓይነት ጥርጥር እንዳያድርበት እግዚአብሄር ለሳዖል ከቁ2-5 ውስጥ ለማረጋገጫነት የሰጣቸው ሶስቱን ዋና ዋና ምልክቶች ምን ምን እንደሆኑ በመዘርዘር ተናገር። ቁ7 ላይ ሳዖል ማድረግ ያለበትን ነገር ለማድረግ ቅድመ ሁኔታ ሆነው የተነገሩት ነገሮች የትኞቹ ናቸው?
3. ቁነ-16 ላይ ስንመለከት የሳዖል አጎት ሳዖልን ሁለት ጥያቄዎች ሲጠይቀው እናነባለን። አጎትየው የጠየቃቸው ሁለት ጥያቄዎች ምንና ምን የሚሉ ናቸው? ሳዖል ለተጠየቀው ጥያቄዎች ሁሉ የተሟላ መልስ ሰጥቷል ብለህ ታምናለህ ወይ? ለምን ይመስልሃል ሳዖል ለአጎቱ ሳሙኤል ስለነገረው የንግስና ነገር መንገር ያልፈለገው?
4. ቁ17-19 ላይ ሳሙኤል ለህዝቡ እግዚአብሄር ያደረገላቸውንና ህዝቡ ደግሞ ያደረጉትን ጥፋጥ ይነግራቸዋል። ንጉስ ተመርጦላቸው እያለ ለምንድነው ቀድሞ የነገራቸውን ነገር እንደገና አንስቶ የሚናገራቸው? ቁ20-23ትንና ሳዖል ያለፈባቸውን ሁኔታዎች ሁሉ ስትመለከት፤ ንግስና ሳዖል ፈልጎና ተሯሩጦ ያገኘው ነገር ነው ብለህ ታምናለህ ወይስ ንግስና ነው ሳዖልን ተከታትሎ ያገኘው? አንተስ የከፍታ ሥፍራ ፈልጎ የሚያገኝህ ሰው ነህ ወይስ በሰውም ላይ ተረጋግጠህ ቢሆን ከፍ ለማለት የማትመለስ ነህ?
5. ቁ23-24 ሳሙኤል ሳዖልን ከህዝቡ ጋራ ሲያነጻጽረው የምንመለከተው ከምን አንጻር ነው? በዚያው ክፍል ውስጥ ህዝቡ ንጉሳቸውን አይተው ሲጮሁ እንመለከታለን። ህዝቡንስ ያስጮኸው ነገር ምንድነው? እግዚአብሄር ለህዝቡ ቢመርጥና የእግዚአብሄር ምርጫ ቢሆን ምን የተለየ ነገር ያደርግ ይመስልሃል?
6. ቁ26-27 ላይ የሰፈረውን ሃሳብ ስናነብ በሁለት ዓይነት የተከፈሉ ሰዎችን እናያለን፤ የእነዚህን ሁለት ዓይነት ሰዎች ማንነት ተናገር። ከእግዚአብሄር ንጉስ ጠይቀው፣ እግዚአብሄርም በተለያየ መንገድም ምርጫውን አረጋግጦላቸው እያለ፤ ንጉሱን ለመቀበል እንቢተኞች ሰዎች መገኘታቸው ምን ሊያስተምረን ይችላል ትላለህ? ለእንቢተኞቹ ያሳየው ምላሽስ ምን ያስተምረናል?
7. ሳዖል በእግዚአብሄር የተመረጠና የተቀባ መሆኑ፣ ቁመናው ያማረና ረጅም፣ በመንፈስ የተሞላ፣ የነብዩ ሳሙኤል ድጋፍ ያለው፣ የአብዛኛ ህዝብ ድጋፍ ያለው ነው፣ እግዚአብሄር ልባቸውን የነካቸውና ሃያላን ሰዎች የተቀበሉት ሰው መሆኑ፤ ሳዖል በትክክለኛ መንገድ ለመሄዱ ዋስትና ሆኖታል ወይ? ለምን ይህንን እንዳልክ አስረዳ።
8. ቁ9-10ርን ስናነብ የሳዖል ልብ እንደተለወጠ እንመለከታለን። መቼ ነበረ የሳዖል ልብ የተለወጠው? ለምን ይመስልሃል እግዚአብሄር የሳዖልን ልብ ለመቀየር ከሳሙኤል እስኪለይ ድረስ መጠበቅ የፈለገው ብለህ ታምናለህ? አንተስ የሰዎችን ልብ ለመቀየር ሞክረህ ታውቃለህ ወይ? በሰዎች ህይወት ማለትም በትዳር ጓደኞቻችን፣ በልጆቻችን፣ በጓደኞቻችንና በሌሎችም ህይወት ውስጥ የተለያዩ ብዙ አስተዋጽዖዎችን ማድረግ እንደምንችል የታወቀ ቢሆንም እንኳን፤ የሰዎች ልብ የመቀየሩ ችሎታ ያለው እግዚአብሄር ብቻ መሆኑን ልንረዳ ያስፈልገናል።

# <u>ጥናት አስር 1ኛ ሳሙ 11፡1-15</u>

የጥናት ዓላማ፡- እግዚአብሄር በአንዳችን ህይወት የሚሰራበት መንገድ በሌላችን ውስጥ ከሚሰራበት የተለየ ሊሆን ስለሚችል፤ አንዳችን ከተለማመድነው አሰራር ውጭ እግዚአብሄር ሌላ ዓይነት አሰራር ሊኖር አይችልም ከሚለው ግትር አመለካከታችን ልንላቀቅ እንደሚገባን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "እግዚአብሄር ጌዴዎንን እንዲህ አለው፤ አሁንም ሰዎቹ ብዙ ናቸው ወደ ወንዝ ይዘሃቸው ውረድ በዚያም እለይልሃለሁ።" መሳ 7፡4 "...ቁጥራቸውም ከእስራኤል ሶስት መቶ ሺህ፣ ከይሁዳም ሰላሳ ሺህ ነበር።" 1ኛ ሳሙ 11፡8

1. 1ኛ ሳሙ 11፡1-15 በአንድነት ይነበብ። በቁ1 ላይ ስናነብ ይህ ናዖስ የተባለው የአሞን ንጉስ ኢያቢስ ገለዓድን መጥቶ ሲከባት የኢያቢስ ገለዓድ ሰዎች ምላሽ ምን ነበረ? ከኢያቢስ ገለዓድ ሰዎች መሃል ለናዖስ ለመገዛት ፈቃደኛነታቸውን ያረጋገጡት የሰዎች ቁጥር ምን ያህል ነበረ? የኢያቢስ ገለዓድ ሰዎች ከአሞን ሰዎች ጋራ ሊገቡ ፈቃደኛነታቸውን የገለጹለት ቃል ኪዳን ያዘለው ነገር ምን ነበረ?
2. ቁ2ትን ስናነብ አሞናዊው ናዖስ የኢያቢስ ገለዓድ ሰዎች ላቀረቡትለት የድርድር ሃሳብ ምላሹ ምን እንደነበረ ተናገርር? ናዖስ ይህንን ከባድ የሆነውን አይን እስከማውጣት የሚደርሰውን የድፍረት ጥያቄ ለመጠየቅ የልብ ልብ የሰጠው ነገር ምንድነው ብለህ ታስባለህ? የኢያቢስ ገለዓድን ሰዎች አካሄድና የናዖስን ደግሞ የድፍረት ጥያቄ ስንመለከት የእኛ ጠላት ስለሆነው ስለሰይጣን አሰራርና እኛ ደግሞ ማድረግ ስለሚኖርብን ጥንቃቄ ምን ያስተምረናል?
3. ቁ3-4 ላይ ስናነብ የኢያቢስ ሰዎች የነገሩ እየባሰ መምጣት ምን እንዲያደርጉ ነው የገፋቸው? ክፍሉን ወረድ ብለን ስናነብ፤ ከፊታቸው ስለተደቀነው አደጋ ከወንድሞቻቸው እርዳታንና መፍትሄን ለመፈለግ በመጠየቃቸው አይናቸውን ከማጣትና ከባርነት እንዳተረፉ እናያለን። ለብቻቸው ጠላታቸውን ከመጋፈጥ ይልቅ የወንድሞቻቸውን እርዳታ ለመጠየቅ መወሰናቸውን ስናይ፤ እኛ ከእነርሱ ድርጊትና ከውጤቱ ምን መማር እንችላለን?
4. በኢያቢስ ሰዎች ተልከው ወደ ጊብዓ የመጡት ሰዎች መልዕክቱን በተናገሩ ጊዜ ሰሚው ህዝብ የወሰደው እርምጃ ምን ነበረ? ሳዖል ከኢያቢስ ሰዎች የመጣውን ዜና በሰማ ጊዜ የተሰማውን ስሜት፣ በውስጡ የሆነውን ነገርና ከዚያም በኋላ የወሰደውን እርምጃ አስመልክቶ የሆነውን ነገር ተናገር።
5. ቁ9-11ን በማንበብ ከኢያቢስ ገለዓድ የተላኩት መልዕክተኞች ይዘው የተመለሱት መልስ ምን የሚል ነበረ? መልዕክተኞቹ ይዘው የመጡትን ምላሽ በሰማ ጊዜ የኢያቢስ ገለዓድ ህዝብ ስሜቱን በምን ዓይነት ነው የገለጠው?
6. ቁ12-13 ትን ስንመለከት ይህንን ጦርነት በመጠቀም እግዚአብሄር የሳዖልን ንግሥና አስመልክቶ የሰራው ምን ነገር ታያለህ? በነዚህ ቁጥሮች ውስጥስ ስለ ሳዖል ንግሥና አጀማመር በመልካም መንፈስ እንደጀመረ የሚጠቁመን የትኛው ሃሳብ ነው?
7. 1ኛ ሳሙ 10፡1ድን ስንመለከት ሳዖል በእግዚአብሄር የተቀባ እንደሆነ፤ በ10፡24 ላይ ደግሞ አብዛኛው ህዝብ የሳዖልን ንግስና የተቀበለ እንደሆነ እንመለከታለን፤ ታዲያ በዚህ ክፍል ማለትም በቁ14-15 ውስጥ እንደገና የሳዖልን ንግስና ማጽናት ያስፈለገበት ምክንያት ለምንድነው?
8. በመሳፍንት ምዕራፍ 7 ላይ ስናነብ፤ ጌዴዎን ምድያማውያንን ለመውጋት ሰላሳ ሁለት ሺህ ወታደሮች ይዞ ሊሄድ ሲነሳ እግዚአብሄር የሰራዊቱን ቁጥር እንዲቀንስ ሲነግረው እናያለን። ታዲያ በዚህ በ1ኛ ሳሙ 11፡8 ላይ ሳኦል ሶስት መቶ ሰላሳ ሺህ ወታደር ሲያሰልፍ እንዲቀንስ ያልታዘዘው ለምንድነው ብለህ ታምናለህ? እግዚአብሄር እርሱ አምላክ ስለሆነና ፈቃዱን ለመፈጸም የወደደውን መንገድ ስለሚጠቀም፤ እኛን በግላችን ያለማመደን መንገድ እንዳለ ሁሉ፤ ሌሎች ደግሞ ሌላ አይነት ልምምድ ሊኖራቸው እንደሚችል ልንገነዘብ ይገባናል።

# ጥናት አስራ አንድ 1ኛ ሳሙ 12፡1-25

የጥናት ዓላማ፡- እግዚአብሄር አምላክ እኛን ልጆቹና ህዝቡ ያደረገን ምክንያት በእኛ ስላየው ነገር ሳይሆን እርሱ ራሱ ስለ ወደደን ብቻ ሲሆን፤ የእርሱ ካደረገንም በኋላ እንደዋዛ ነገር እንደማይተወን ልንገነዘብ ያስፈልገናል።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "እግዚአብሄር የራሱ ህዝብ ያደርጋችሁ ዘንድ ስለወደደ፤ ስለታላቅ ስሙ ሲል እግዚአብሄር ህዝቡን አይተውም።" 1 ሳሙ 12፡22

1. 1ኛ ሳሙ 12፡1-25 በአንድነት ይነበብ። በቁ1-7 ላይ ሳሙኤል የራሱን ህይወት አስመልክቶ ለህዝቡ ሊናገር የፈለገውን ሃሳብ በአንድ አጠር ባለ አረፍተ ነገር ተናገር። ሳሙኤል የራሱን አገልግሎት በመገምገም ለህዝቡ የተናገረው በህዝቡ ዘንድ የነበረው ተቀባይነት ምን ይመስላል? አንተስ ሳሙኤል የተናገረውን አይነት አፍህን ሞልተህ መናገር ትችላለህ ወይ?
2. በቁ8 ላይ እስራኤል በግብጽ በባርነት በነበረበት ዘመን የሆነውን ነገር ይነግረናል። እግዚአብሄር ለህዝቡ መፍትሔ የሚሆን ነገር እንዲሰጥ ህዝቡ ምን ማድረግ ነበረበት? የእስራኤል ሕዝብ ወደ እግዚአብሄር ለእርዳታ በጮኸበት ጊዜ በመፍትሄነት የተላከለት ነገር ምን ነበረ? አብዛኛውን ጊዜ ለጩኸታችን መልስ አድርጎ እግዚአብሄር የሚጠቀመው በአጠገባችን ያሉትን ሰዎች እንደሆነ ምን ያህል ተገንዝበናል?
3. ቁ9-11 ስናነብ አምላካቸውን የረሱትን ህዝቦች መልሰው እንዲያስታውሱት እግዚአብሄር የተጠቀመበት መንገድ ምን ነበረ? በጠላቶቻቸው በተወጉና በተቸገሩ ጊዜ እግዚአብሄር ከነዚህ ጠላቶቻቸው እንዲታደጋቸው ወደርሱ ሲጮሁ የገቡት ቃል ኪዳን ምን ነበረ? እግዚአብሄርስ ለዚህ ምን ዓይነት እርምጃ ሲወስድ ነው የምናየው?
4. የመሳፍንትን መጽሃፍ ስንመለከት እግዚአብሄር ህዝቡን ለመታደግ ቢያንስ አስራ ሁለት የሚያድናቸው ሰዎች እንዳስነሳላቸው እናያለን። በቁ11 ላይ የተዘረዘሩትን ጨምሮ አስራ ሁለት ያህል መሳፍንት መላኩ፤ ህዝቡ ቃል ኪዳናቸውን እንዳልጠበቁ እንዴት ያሳየናል? ቢያንስ አስራ ሁለት ጊዜ ለጠላቶቻቸው አልፈው ተሰጥተው ያንኑ ያህል ጊዜ ደግሞ አድኗቸዋል። ይህ የእግዚአብሄር አድራጎት ስለ ሰው ልጆች ባህርይ ምን ያስተምረናል? ስለ እግዚአብሄርስ ምን መማር እንችላለን?
5. 12-15 ትን ስናነብ የእስራኤል ህዝብ እግዚአብሄር ንጉሳችን ከሚሆን ሌላ በፊታችን ልናየው የምንችለው ንጉስ ይሰጠን እንዳሉና እግዚአብሄርም የጠየቁትን እንደሰጣቸው እናያለን። እስራኤል ንጉሳቸውንም ጨምሮ ለወደፊት መልካም እንዲሆንላቸውና ከአምላካቸው ጋራ በመስማማት መኖር እንዲችሉ ከፈለጉ ማድረግ የሚገባቸውን ቢያንስ አምስት ነገሮች ዘርዝር። በቁ14-15 ላይ የምንመለከተው ዓይነት ቃል ኪዳን ምን ዓይነት ቃል ኪዳን ነው የሚባለው?
6. ነብዩ ሳሙኤል በቁ16-19 ላይ ዝናብ መዝነብ በማይገባው ጊዜ ዝናብና ነጎድጓድን የማድረግ ተአምራት በህዝቡ መሃል በማድረግ ሊያረጋግጥላቸው የፈለገው አንድ እውነት ምን ነበረ? በተለይም ቁ19ን አተኩረን ስንመለከት እነዚህ ሰዎች ባደረጉት ነገር እግዚአብሄርን በመበደላቸው ጸጸት ተሰምቷቸው ነው ወይ ሳሙኤልን እንዲጸልይላቸው የጠየቁት ወይስ ከዚህ የተለየ ምክንያት ታያለህ?
7. ቁ20-21 ሳሙኤል ህዝቡን "አትፍሩ" በማለት ሲያጽናናቸውና ሲያበረታታቸው እናያለን። የሳሙኤል ማጽናናት ሃጥያታቸውን እየሸፋፈነ ነው ወይ? ይህንን ለማለት እንዴት እንደቻልክ አስረዳ። ለእነዚህ እስራኤላውያን ሳሙኤል በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የሚመክራቸው ሁለት መሰረታዊ የሆኑ ምክሮችን ሲሰጣቸው ይታያል። እነዚህ ሁለት ምክሮች ምንና ምንድናቸው?
8. ቁጥር 22-25 ላይ እስራኤል የእግዚአብሄር ህዝብ ሊሆን ስለቻለበት ምክንያት ይህ ክፍል ምን ይነግረናል? ደግሞስ እግዚአብሄር ህዝቡን ስለማይተውበት ምክንያት ክፍሉ የሚነግረን ነገር ምንድነው? አንተስ የእግዚአብሄር ልጅ ለመሆን የበቃኸው ከእግዚአብሄር ፍቅር የተነሳ እንደሆነና በሃጥያትህ እንዳትጠፋ የማይተውህ ስለ ታላቅ ስሙ ሲል እንደሆነ በእውነት ከልበህ ገብቶሃል ወይ?

## ጥናት አስራ ሁለት 1ኛ ሳሙ 13፡1-22

የጥናት ዓላማ፡- በሥጋዊ ዓይኖቻቸው ብቻ የሚተማመኑ ሰዎች አስቸጋሪ የሆኑ አጣብቂኞች ውስጥ በሚገቡበት ወቅት የሚወስዱት እርምጃ እግዚአብሄርን የሚያሳዝን ነው፤ ስለዚህም እንደ ነብዩ ኤልሳ የማይታየውን የምናይበት የእምነት ዓይኖቻችንን እንዲከፍትልን መንፈስ ቅዱስን መለመን ይኖርብናል ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ኤልሳም፤ እግዚአብሄር ሆይ ያይ ዘንድ እባክህ ዓይኖቹን ክፈትለት በሎ ጸለየ፤ እግዚአብሄርም የአገልጋዩን ዓይኖች ከፈተለት ...አየ።" 2ኛ ነገ 6፡17

1. 1 ሳሙ 13፡13፡1-22 በአንድነት ይነበብ። እስራኤል በፍልስጤማውያን ቁጥጥር ስር እንደነበሩና ያሏቸውን ያደርጉ እንደነበረ ቁ19 ላይ እናነባለን። ቁ1-4 ላይ ስናነብ ከዚህ ሁኔታቸው ለመውጣት ውሳኔ አድርገው ለጦርነት ሲዘጋጁ ቁ4 ላይ ጠላቶቻቸው ስለተሰማቸው ስሜት ምን ይነግረናል? ይህ ሁኔታ በእኛና በጠላታችን መሃል ሊኖር ስለሚችለው ሁኔታ ምን ሊያስተምረን ይችላል ብለህ ታምናለህ?
2. የእስራኤል ህዝብ ንጉስ እንዲያነግስላቸው ሳሙኤልን በ1ኛ ሳሙኤል ምዕራፍ 8 በተለይም ቁ19-20 ላይ ሲጠይቁ "የሚመራንና ከፊታችን የሚሄድ፣ ጦርነታችንንም የሚዋጋልን ንጉስ.." በማለት ነበረ ጠይቀው ሳዖል የተሰጣቸው። ታዲያ በዚህ በቁ5-7 ላይ ሲሆን የምናየው ክስተት ሊያረጋግጥላቸው የቻለው አንድ እውነት ምንድነው ትላለህ? በአንተ ህይወትስ፤ ይህንን ወይም ያንንን ባገኝ ህይወቴ የተሳካ ይሆናል ብለህ የምታምነው ነገር አለወይ? ከነዚህ ሰዎች ህይወት ምን መማር እንችላለን?
3. በቁ6 ላይ "እስራኤላውያን ያሉበት ሁኔታ እጅግ የሚያሰጋ መሆኑንና ሰራዊታቸውም በከባድ ጭንቀት ውስጥ መግባቱን ባዩ ጊዜ" ሲል ያዩት ነገር ምን ነበረ? የሁኔታውን አስከፊነት የተመለከተው ይህ የእስራኤል ህዝብ የወሰደው እርምጃ ምን ነበረ?
4. በቁ4 ላይ ሕዝቡ ሳዖልን ለመከተል እንደተሰበሰቡ ሲነግረን፤ ቁ8ትን ደግሞ ስናነብ የተሰበሰበው ህዝብ እንደተበተነ ይነግረናል። ንጉሱ ሳዖል በ4 ላይ ተከታዮችን ለማግኘት ያልተቸገረበት እና በቁ8 ላይ ግን አብረውት ሊቆሙ የሚችሉ ብዛት ያላቸው ሰዎች ማግኘት የተቸገረበት ምክንያት ለምንድነው ብለህ ታምናለህ? በዚህ ክፍል ከሆነው ሁኔታ መማር የምንችለው ነገር ካለ ጥቂት ሰዎች ሃሳባቸውን እንዲናገሩ ይደረግ።
5. ከቁ8-11 ላይ ስትመለከት፤ ካህን እንጂ ንጉስ ሊሰራው የማይገባውን መስዋዕት የማቅረብ ድርጊት ለመፈጸም ሳዖልን ያስገደደው ነገር ምን ነበረ? መስዋዕቱን ባቀረበበት ሰዓትና ሳሙኤል በመጣበት መሃል ስለነበረው የሰዓት ልዩነት ክፍሉ የሚነግረን ነገር ምንድነው? ሳዖል አጣብቂኝ ውስጥ በገባበት ሰዓት የወሰደውን እርምጃና ኢዮሳፍጥ በ2ኛ ዜና 20-1-4 ላይ አጣብቂኝ ውስጥ በገባ ጊዜ በወሰደው እርምጃ መሃል ምን ልዩነት እንደምታይ ተናገር።
6. ቁ12-15ትን ስናነብ፤ የሚቃጠል መስዋዕት ማቅረቡን አስመልክቶ በሳዖልና በሳሙኤል መሃል የምንመለከተው የአመለካከት ልዩነት ምንድነው? ሳዖል የእግዚአብሄርን ህግ አለመጠበቁና የማይገባውን ለማድረግ መድፈሩ በህይወቱ ላይ ያስከተለው ነገር ምን ታያለህ?
7. ቁ19-22 የእስራኤል ጠላት ማለትም ፍልስጤማውያን በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ስንመለከት እስራኤልን በባርነት ለማቆየት የተጠቀሙበት ስልት ምን ነበረ? ያለጦር ዕቃ የጦር ሜዳ ላይ መገኘት አደገኛ መሆኑን የተረዳው ጳውሎስ ይህንን አስመልክቶ በኤፌሶን 6 ውስጥ ለክርስትያኖች የሚመክረው ምክር ምን በማለት ነው? አንተስ፤ ጠላትህ የተሰጠህን የጦር ዕቃ ለብሰህ እንዳትገኝ እንደሚፈልግ ተረድተሃል ወይ?
8. ቁ6 ስለህዝቡ ሲናገር በፍርሃት የቀለጡት "ባዩ ጊዜ በየዋሻው...ተደበቁ"፣ ስለሳዖል ደግሞ የማይገባውን ወደማድረግ ያስገባው ነገር ቁ11 "አየሁ...ስለዚህ ማድረግ ግድ ሆነብኝ" እያለ ሲናገር፣ በ2ኛ ነገ 6፡15 ላይ ደግሞ የነብዩ የኤልሳ ሎሌ በሥጋ ዓይኖቹ ሲመለት በፍርሃት እንደተሞላ እናያለን። ለዚህ ችግር መጽሃፍ ቅዱሳችን በተለይም በ2ኛ ነገ 6 ውስጥ መፍትሄ አድርጎ የሚሰጠው ነገር ምንድነው? አንተስ ነገሮችን የምትመለከተው በየትኛው ዓይንህ ይሆን?

# ጥናት አስራ ሶስት 1ኛ ሳሙ 14፡1-52

የጥናት ዓላማ፡- በአንዱ በዮናታን እምነት ብዙዎች በጠላት ፍርሃት እስረኛ ሆነው የተቀመጡት ተፈትተው ወደጦርነቱ እንደተቀላቀሉ ሁሉ፤ እኛም በእግዚአብሄር በመታመን ስንወጣ የብዙዎችን ልብ ማንቃታትና የወደቀውን ልባቸውን ማንሳት እንደምንችል ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "እነዚያ ቀድሞ ከፍልስጤማውያን ጎን ተሰልፈው የነበሩትና አብረዋቸው ወደሰፈራቸው የወጡት ዕብራውያን ከሳዖልና ከዮናታን ጋራ ወደ ነበሩት እስራኤላውያን ገቡ። በኮረብታማው የኤፍሬም አገር ተሸሽገው የነበሩት እስራኤላውያን ሁሉ...አጥብቀው በመከታተል አሳደዷቸው።" 1 ሳሙ 14፡21-22

1. 1ሳሙ 14፡1-52 በአንድነት ይነበብ። በ1ኛ ሳሙ 13፡22 ላይ ከእስራኤል ሁሉ መሃል ሰይፍ ወይም ጦር ከሳዖልና ከዮናታን ውጭ ማንም እንዳልነበረው እናነባለን። ይህ እስራኤል የሚገኝበት ሁኔታ ጦርነት ተዋግቶ ለማሸነፍ እስራኤል ምን ያህል ዕድል ነበረው ትላለህ? ቁ1 ላይ ስናይ ዮናታን ወደፍልስጤማውያን ሲወጣ ላባቱ እንዳልነገረው እናነባለን፤ ለአባቱ ሳይናገር መሄድ የፈለገበት ምክንያት ለምን ይመስልሃል?
2. በቁ6 ላይ "...ምናልባትም እግዚአብሄር ይዋጋልን ይሆናል፤ በብዙም ሆነ በጥቂት ለማዳን እግዚአብሄርን የሚያገደው የለምና አለው" ከሚለው የዮናታን አንጋገር ስትመለከት እርግጠኛ ሆኖ ሳይጠራጠር ለጋሻ ጃግሬው ሊያረጋግጥለት የፈለገው አንድ እውነት ምን ነበረ? በዚሁ ንግግር ውስጥ ደግሞ ስንመለከት ለራሱም ቢሆን ሙሉ ለሙሉ እርግጠኛ ለመሆን ያልቻለ የሚመስልበት አነጋገር የተናገረው ምንን አስመልክቶ ነው?
3. ቁ7-14 ትን ስናይ ዮናታን እግዚአብሄር በዚህ ውግያ ላይ ድል ሊሰጣቸው መፍቀዱንና አለመፍቀዱን አላወቀም ነበረ ከተባለ፤ በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ዮናታን የእግዚአብሄርን ፈቃድ ተረድቷል ማለት እንችላለን ወይ? ከሆነስ ፈቃዱን ለማወቅ የተጠቀመበት መንገድ ምን ነበረ? ዮናታን እግዚአብሄር በብዙም ሆነ በጥቂት ማዳን እንደሚችል ብቻ ሳይሆን በራሱና በጋሻ ጃግሬው እስራኤልን ከፍልስጤም እንደሚያድን እርግጠኛ መሆኑን የተናገረበት ክፍል የትኛው ነው?
4. በቁ20-23 ላይ የምናያቸው በሶስት የተለያዩ ቡድኖች ውስጥ የተከፈሉ እስራኤላውያንን እንመለከታለን፤ እነዚህ ሶስቱ የምታያቸው ቡድኖች የትኞቹ እንደሆኑ ተናገር።
5. ቁ24-35 የእስራኤል ህዝብ ስለነበረበት ሁኔታ እነዚህ ቁጥሮች ምን ይነግሩናል? ይህ ሁኔታ እንዲከሰት ምክንያት የሆነው ሰው ማን ነበረ? ዮናታን የሆነውን ነገር በተመለከተና ከህዝቡም ከሰማ በኋላ አባቱ በዚህ ቀን በወሰደው እርምጃ ምክንያት በደረሰው ነገር ሲሰጥ የምንሰማው አስተያየት ምን የሚል ነው?
6. ቁ36-44 በተለይም ቁ36 ላይ ሲታይ ፍልስጤማውያንን ተከትሎ መምታትን አስመልክቶ ሶስት ዓይነት የተለያዩ አመለካከት ያላቸውን ሰዎች እንመለከታለን፤ እነዚህ ሶስት አመለካከቶች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር። አንተስ ማድረግ የሚኖርብህ ነገር ሲኖር እንደካህኑ እግዚአብሄርን ወደ መጠየቅ ልብህ ያዘነብላል ወይስ እንደ ሳዖል ተነስቼ ልውጣ ማለት ይቀድምሃል?
7. ቁ45-52 በአንድነት ይነበብ። ቁ45 ላይ ስናነብ የእስራኤል ህዝብ ሁሉ የዮናታንን መገደል በመቃወም ሳዖልን ሲቃወሙት እናያለን፡፡ መገደል የለበትም በማለት የሰጧቸው ሁለት ምክንያቶች ምንና ምን ነበሩ? "ይህንን ያደረገው በእግዚአብሄር እርዳታ ስለሆነ..." በማለት ሲናገሩ በእግዚአብሄር እርዳታ ማድረጉ ለምንድነው እንዳይሞት ምክንያት ሊሆን የሚችለው?
8. ከ20-23 ያለውን ክፍል ወደኋላ ተመልሰ ስንመለከት ሳዖልና በተለያየ መንገድ ሸሽቶ የነበረው ህዝብ ሁሉ ወደጦር ሜዳ ተመልሶ ምርኮን ለመበዝበዝ እንዲበቃ ምክንያት የሆነው ሰው ማነው ብለህ ታምናለህ? አንተስ በፍርሃትና በተለያየ ምክንያት ከወንጌል ጦር ሜዳ ሸሽቶ ለተደበቀው ሰው ሁሉ በእግዚአብሄር ላይ በምታሳየው ቆራጥ እምነት ምክንያት ድፍረት አግኝተው እንደሚመለሱ ትረዳለህ ወይ? የአንዳችን ጥንካሬና ቆራጥነት የሌሎችን እምነት ሊገነባ እንደሚችል ልንገነዘብ ያስፈልገናል።

# ጥናት አስራ አራት 1ኛ ሳሙ 15፡1-35

የጥናት ዓላማ፡- ሳዖል እግዚአብሄርን ባለመታዘዝ ላደረጋቸው ነገሮች በአምላኩ ፊት ራሱን አዋርዶ በንስሃ መቅረብ ሲገባው ሃጥያቱን በሌሎች ሰዎች ላይ ማላከክ መሞከሩ ዙፋኑን ለማጣት እንዳደረሰው ሁሉ፤ እኛም ሐጥያታችንን የሌሎች ሃጥያት አድርገን ራሳችንን ነጻ ለማውጣት በመሞከር እግዚአብሄርን የማታለል ሙከራ ለማድረግ እንዳንሞክር ለማስገንዘብ።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- “ሐጥያት ሰርቻለሁ፤ የእግዚአብሄርን ትዕዛዝና የአንተን መመሪያ ጥሻለሁ፤ ህዝቡን ፈርቼ ስለነበር የጠየቁኝን ታዝዣለሁ።” 1ኛ ሳሙ 15፡24 ቁ15ትንም ማንበብ ይጠቅማል።

1. 1ኛ ሳሙ 15፡1-35 በአንድነት ይነበብ። በቁ1-3 ላይ ስናነብ እግዚአብሄር አማሌቅን ጨርሶ ለማጥፋት የወሰነበት ምክንያት ለምን ነበረ? ለሳዖል የእግዚአብሄር ትዕዛዝ ቀጥተኛና የማያሻማ ነበር ማለት የሚቻለው ለምንድነው?
2. ቁ4-6 ቄናውያን ከአማሌቃውያን ልዩ የሚያደርጋቸው አንድ ነገር ምን ታያለህ? ቄናውያን የአማሌቃውያን እድል ፈንታ እንዳይደርስባቸው ማድረግ የነበረባቸው ነገር ምን ነበረ?
3. ቁ7-9 የሳዖል የመጀመሪያው አለመታዘዝ ሆኖ የምናገኘው ነገር ምንድነው? በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ከምንመለከተው ነጉሱ ሳዖል መጥፋት አለባቸው ብሎ በራሱ የወሰናቸውና በሌላ በኩል ደግሞ መጥፋት አይኖርባቸውም በማለት ለመተው የወሰናቸው ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር። ሳዖል እግዚአብሄርን ያልታዘዘበት ምክንያት ካለማወቅና ትዕዛዙን ካለመረዳት የተነሳ አለመሆኑን ከዚህ ምንባብ ውስጥ የሚነግረን የትኛው ክፍል ነው?
4. ቁ10-13 በአንድነት ይነበብና በተለይ ቁ12ትን ስናነብ ሳዖል ምን ሲያደርግ ነው የምንመለከተው? ይህንን መታሰቢያ ለመስራት ለውሳኔ ያደረሰው ትልቅ ነገር ምንድነው ብለህ ታምናለህ? ቁ11ድንና ቁ13ትን ላይ እግዚአብሄርና ሳዖል ለሳሙኤል በሚናገሩት ነገር ልዩነትን ታያለህ ወይ? ልዩነታቸው ምን እንደሆነ ተናገር።
5. በቁ15 ላይ ሳዖል ለሳሙኤል ጥያቄ በሰጠው መልስ ላይ ስንመለከት፤ አለመታዘዝ ሆኖ ላያቸው ነገሮች ማለተም ከአማሌቃውያን ማርኮ ማምጣትንና ሳይገድሉ የመተውን ነገር በተመለከተ ተጠያቂ ያደረገው ማንን ነው? በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሄር መታዘዝ በሚመስለው ነገርስ እነማንን ነው አስገብቶ የተናገረው? በአንተስ ህይወት ክፉ አድራጊዎች ሁልጊዜ ሌሎች፤ መልካም መልካሙ ነገር ላይ ግን እንደምንም ራስህን የምትጨምርበት ጊዜ ይኖር ይሆን?
6. ቁ16-19 ላይ እግዚአብሄር ትናንት ማታ ነገረኝ ብሎ ከሚናገረው መሃል፤ ሳዖል በእግዚአብሄር ፊት ሃጥያት የሆነውን ነገር ለማድረግ ምክንያት የሆነውን ነገር እንዴት በማለት ነው የሚገልጸው? ቁ22 ስትመለከት፤ እግዚአብሄር በሚቃጠል ቁርባንና መስዋዕት ደስ አይለውም ማለቱ ነው? ካልሆነስ ይህ የሳሙኤል አነጋገር ምን ማለት እንደሆነ ነው የምትረዳው?
7. ቁ26-35ን በመመልከት ሳሙኤል ከሳዖል ጋራ ለመመለስ እንቢ ያለበትን ምክንያት በሁለት አረፍተ ነገሮች ጨርሶታል፤ እነዚህ ሁለት አረፍተ ነገሮች ምን እንደሆኑ ተናገር። ከነዚህ ቁጥሮች ስትረዳ ንጉሱ ሳዖል ከእግዚአብሄር ክብር በላይ ክብርን ሲፈላለግ የምናየው ከማን ነው?
8. ቁ24 ላይ ሳዖል እግዚአብሄርንና ሳሙኤልን እንደበደለ አድርጎ ሲናገር አሁንም ለሃጥያቱ ምክንያት አድርጎ የሚናገረው ማንን ነው? “ህዝቡን ፈርቼ ስለነበረ የጠየቁኝን ታዝዣለሁ።” የሚለው አነጋገሩ በእግዚአብሄር ዘንድስ ተቀባይነት አግኝቷል ብለህ ታምናለህ ወይ? አንተስ በህይወትህ እግዚአብሄርን ላለመታዘዝህ ሰዎችን ምክንያት አድርገህ ታውቃለህ ወይ? እግዚአብሄር በሃጥያታችን አምነንና ተጸጽተን መናዘዛችን እንጂ በሰዎች ላይ ማላከካችን እንደማይማርከው ልንረዳ ያስፈልገናል።

# ጥናት አስራ አምስት 1ኛ ሳሙ 16፡1-23

የጥናት ዓላማ፡- ሳሙኤል የተከበረና የተናገረው ነገር በምድር ላይ የማይወድቅ ነብይ ቢሆንም እንኳን፤ ሰው እንደሚያይ እግዚአብሄር እንደማያይ እግረ መንገዱን እንዳስተማረው ሁሉ፤ ብዙ ነገር የምናውቅና የእግዚአብሄር ነገር የገባን አድርገር ራሳችንን ብንቆጥርም እንኳን ከእግዚአብሄር ለመማር ልባችንን ክፍት አድርገን መጠበቅ እንደሚኖርብን ለመማር።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- “መልኩን ወይም ቁመቱን አትይ፤ እኔ ንቄዋለሁና። እግዚአብሄር የሚያየው ሰው እንደሚያየው አይደለም። ሰው የውጭውን ገጽታ ያያል፤ እግዚአብሄር ግን ልብን ያያል አለው።” 1ኛ ሳሙ 16፡7

1. 1ኛ ሳሙ 16፡1-23 በአንድነት ይነበብ። በቁ1-2 ላይ ስናነብ እግዚአብሄር ነብዩን ሳሙኤልን ያነጋገረባቸው ሁለት ርዕሶች ምንና ምንድናቸው? ከእነዚህ ሁለት ርዕሶች መካከል ለሳሙኤል አጠያያቂ ሆኖ የተገኘው የትኛው ነው? የሳሙኤልን ፍርሃት የተመለከተው እግዚአብሄር የወሰደው እርምጃ ምን ነበረ? እኛም ብንሆን ፍርሃታችን የማይረዳልን አምላክ ሳይሆን የምናመልከው ለፍርሃታችን መፍትሄን የሚያዘጋጅልን አምላክ ነው ያለን።
2. በቁ3-5 ላይ እግዚአብሄር ለሳሙኤል ተልዕኮ ሲሰጠው ማወቅ ከሚገባው ነገሮች መሃል ያስታወቀው አንድ ነገር ምንድነው? እግዚአብሄር ለሳሙኤል በተለይ ዋነኛ የሆነውንና እዚያ ድረስ የተጓዘበትን፤ ማንን መቀባት እንዳለበት ሊነግረው የወሰነው መቼ እንደሆነ ነው የምናየው? ከዚህ ዓይነቱ የእግዚአብሄር አሰራር ለራሳችን ህይወት ምን መማር እንችላለን?
3. ቁ6-7 ላይ ሳሙኤል መልክና ቁመና የነበረውን ኤልያብን ለመቀባት በሞመከር መሳሳቱን እንመለከታለን፤ ምናልባት ለዚህ ስህተቱ ስተዋጽዖ አድርጎ ይሆናል ማለት የምንችለው በቀድሞ አገልግሎቱ የተለማመደው ነገር የምታስታውሰው አለ ወይ? በእግዚአብሄርና በሰው አስተያየት መሃል ያለውን ልዩነት ይህ ክፍል ያስተምረናል። በአምላክና በሰው መካከል ያለውን የአመለካከት ልዩነት ይህ ክፍል ምን በማለት ነው የሚያቀርበው?
4. እሴይ በዚህ በቁ8-13 ውስጥ ስንት ልጆች እንዳሉት ታያለህ? የዳዊት አባት እሴይ ልጁን ዳዊትን ለሳሙኤል ለመግለጥ የተጠቀመባቸው ሁለት ሃሳቦች ምንና ምን እንደሆኑ ግለጽ። በቁ11 ላይ ሳሙኤል ከሚናገረው አነጋገር እግዚአብሄር በቁ7 ላይ የነገረው ነገር ውስጡ በትክክል እንደገባና እንደተረዳ የምናውቀው እንዴት ነው?
5. ቁ14-17ትን ስንመለከት ንጉሱ ሳዖል በክፉ መንፈስ ይጨነቅ እንደነበረ ይታያል። ይህ ሁኔታ በሳዖል ህይወት ላይ ሊመጣ ስለቻለበት ምክንያት ክፍሉ ምን ይነግረናል? ንጉሱ ለገጠመው ችግር አገልጋዮቹ ያቀረቡለት መፍትሄ ምን እንደነበረና፤ የሰጡት መፍትሄ ለምን ዘላቂነት የነበረው መፍትሄ እንዳልነበረ አስረዳ።
6. የንጉሱ የሳዖል አገልጋይ በቁ18 ላይ ስለዳዊት ማንነት የሚያውቀውን ሲዘረዝር ምን በማለት ነበረ የገለጸው? ከተዘረዘሩት ነገሮች ሁሉ ዋነኛና ቁልፍ ሆኖ የምታየው የትኛው ነገር ነው?
7. ቁ19-23 ላይ ሳዖል ዳዊትን እንዲልክለት አባቱን እሴይን ለመጠየቅ ለዳዊት ማንነት እንደ መለያ አድርጎ የተጠቀመበት ነገር ምን ነበረ? በምዕራፍ 16 ውስጥ እንዳየነው ዳዊት ለንጉሥነት ተቀብቷል፤ በዚህ ክፍል ግን ስናነብ የንጉስ አገልጋይ ሆኖ ነው ዳዊትን የምናገኘው። ከዚህ ሁኔታ ውስጥ መማር የምንችለው ነገር ምንድነው?
8. ወደ 7 መለስ ብለን ስንመለከት ሳሙኤልን ለዚህ ተልዕኮ ሲልክ “ሂድና ከእሴይ ልጆች መሃል ዳዊት የሚባል የመጨረሻ ልጅ አለ እርሱን ንጉስ እንዲሆን ቀባልኝ” ማለት ይችል እንደነበረ እናውቃለን፤ ውጤቱን ከተመለከትን በኋላ፤ ከእግዚአብሄር የተነገረው ነገር ሙሉ ለሙሉ ግልጽ አለመሆኑ ለሳሙኤል ለመልካም ሆኖለታል ማለት የሚያስችለን ምን ነገር ታያለህ? የክርስትና እድገት የሚቆም ነገር ስላልሆነ አንተም ሌሎችን ስታገለግል የእድገትህ መንገድም እንደሆነ መቀበል ይኖርብሃል።

# ጥናት አስራ ስድስት 1ኛ ሳሙ 17፡1-58

የጥናት ዓላማ፡- በአንዱ በዳዊት በአምላኩ ላይ በመታመኑ ምክንያት የእስራኤል ታሪክ እንደተቀየረ ሁሉ፤ ዛሬም ቢሆን እግዚአብሄር አንድ በፍጹም ልቡ የሚታመንበት ሰው ካገኘ ሁኔታን ሊቀየር እንደሚችል ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- “ዳዊትም ፍልስጤማዊውን እንዲህ አለው፤ አንተ ሰይፍ፣ ጦርና ጭሬ ይዘህ ትመጣብኛለህ፤ እኔ ግን አንተ በተገዳደርከው የእስራኤል ሰራዊት አምላክ በሆነው፤ ሁሉን በሚችል በእግዚአብሄር ስም እመጣብሃለሁ።” 1ኛ ሳሙ 17፡45

1. 1ኛ ሳሙ 17:1-58 በአንድነት ይነበብ። ከቁ1-11 ውስጥ የተካሄደውን ነገር ቅደም ተከተል በያዘ መንገድ አጠር አድርገው አንድ ወይም ሁለት ሰዎች እንዲናገሩ ይደረግ። በቁ4-7 ላይ የምንመለከተው የጎልያድን ትጥቅ ከሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ የሚያስታውስህ ክፍል የትኛው እንደሆነ መጽሐፉንና ቁጥሩን ለመናገር ሞክር። ለጎልያድ ተግዳሮት የሳዖልና የእስራኤል ህዝብ ምላሽ ምን ይመስል እንደነበረ ተናገር።
2. ቁ12-19 ይነበብ። እስራኤል ለጦርነት ተሰልፎ ባለበት ወቅት ዳዊት የሚገኘው የት ነበረ? በዚህ ክፍል ውስጥ እሴይ ልጁን ዳዊትን ወደ ጦሩ ሰፈር እንዲሄድለት ሲልከው እናነባለን። ምግቡን ለወንድሞቹ ከማድረስ ባሻገር የዳዊት ተልዕኮ ምን ነበረ? ዳዊት የቤተ መንግሥት ነዋሪና ከንጉስ ጋራ የሚኖር ሰው ተመልሶ የአባቱን ከብቶች ለመጠበቅ መመላለሱ ምን ያህል ትሁት ሰው እንደሆነ ይጠቁመናል።
3. ቁ20-25 ዳዊት ከአባቱ እንዲያደር የጠየቀውን ሁለት ነገሮች እንዳከናወነ የምናውቀው እንዴት ነው? ቁ23 ላይ ስናነብ “...ጎልያድ ከሰልፉ መካከል ወጥቶ እንደለመደው ሲደነፋ ዳዊት ሰማ።” በማለት ይነግረናል። የአሁኑን ድንፋታ በተለይም የእስራኤልን ህዝብ አስመልክቶ ልዩ የሚያደርገው ነገር ምንድነው ብለህ ትገምታለህ? አሁንስ ለጎልያድ ተግዳሮት የእስራኤላውያን ምላሽ ምን ሆኖ ነው የምናየው?
4. ቁ26-28 በተለይ ዳዊት በቁ26 ላይ “ውርደት” በማለት የሚጠቅሰው ምኑን ነው? ኤልያብ በቁ28 ላይ ስናነብ በዳዊት ላይ ቁጣው የነደደው ለምን ነበረ? ይህ ሰው ስለዳዊት ልብ የሚናገረውን ሃሳብ በ1ኛ ሳሙ 16፡7 ላይ እግዚአብሄር ስለ ኤልያብ ከሚናገረውና በሐዋ ሥራ 13፡22 ላይ እግዚአብሄር ስለዳዊት የተናገረውን ሃሳብ በማገናዘብ የማነጻጸር ሃሳብህን ስጥበት። እኛስ እግዚአብሄር መልካም ነው ብሎ የተቀበለውን ልብ እንደ ተንኮለኛና ክፉ ልብ አድርገን ስንናገር እንገኝ ይሆን?
5. ቁ29-37ን ስናነብ ሳዖል በቁ33 ላይ “አንተ ገና...” በዚያው ቁጥር ላይ ደግሞ “ሰውየው ግን...” ብሎ “...አትችልም” በማለት ትኩረቱን በምን ላይ እንዲያደርግ ነው ሊያሳየው የሚሞክረው? ቁ34-37 ላይ “ዳዊት ግን...ከአንበሳ መዳፍና ከድብ መንጋጋ ያዳነኝ እግዚአብሄር” በማለት ለሳዖል አስተያየት ከሚሰጠው ምላሽ ትኩረቱ በምን ላይ እንዳለ ነው ማስረዳት የፈለገው?
6. በቁ38-40 ላይ ሳዖል ለዳዊት ሊያለብሰው የሞከረውን የጦር ልብስና የጦር እቃ ለብሶ ለመሄድ ያልሄደበት ምክንያት ለምንድነው? ሳዖል ያስታጠቀውን ትጥቅ ካሆለቀ በኋላ የራሱ የሆነና የተለማመደውን አይነት ትጥቅ ይዞ ሲወጣ ይታያል፤ ይህ ማለት ዳዊት በትርና ወንጭፍ ይዣለሁኝና አሸንፋለሁ በሚል መንፈስ የወጣ ይመስልሃል ወይ? አስረዳ።
7. ጎልያድ በቁ41-51 ውስጥ ስንመለከት ዳዊትን የናቀው ምኑን ተመልክቶ ነው? እነዚህ ሁለት ሰዎች በጦር ሜዳው ውስጥ ይዘው የተሰለፉት ነገር ፈጽሞ የተለያየ እንደሆነ እናያለን፤ የሁለቱንም የጦር እቃ ምን ምን ዓይነት እንደሆነ በመዘርዘር ተናገር። የእነዚህ ሁለት የተለያዩ የጦር እቃዎች በስራ ላይ ውለው ያስገኙት ውጤት ምን ነበረ? አንተስ የጦር እቃህ እንደ ጎልያዱ ሥጋዊ ነው ወይስ እንደተናቀው ዳዊት መንፈሳዊ ነው?
8. ቁ52-58 ላይ “ከዚህ በኋላ የእስራኤልና የይሁዳ ሰዎች ተነስተው እየፎከሩ ፍልስጤማውያንን እስከ ጌት መግቢያና እስከ ኤቅሮን በሮች ድረስ አሳደዷቸው።” በማለት ቁ52 ይጀምራል። ቁ24 ላይ የምናያቸው ሰዎች ከታላቅ ፍርሃት ወደ ፉከራ ስሜት ሊመጡ ምክንያት የሆናቸው ሰው ማነው? እኛም በአምላካችን ላይ በምናሳየው የእምነት እርምጃ ሌሎች የፈሩ እንዲደፍሩና ወደ ጦሩ ሜዳ እንዲመለሱ መርዳት እንችላለን።

# ጥናት አስራ ሰባት 1ኛ ሳሙ 18፡1-30

የጥናት ዓላማ፡- እንደ ዳዊት እግዚአብሄርን በመፍራትና እርሱን በመተማመን፣ በጽድቅ ለመኖር ለቆረጠ ሰው፤ ደጉ እግዚአብሄር አስፈላጊ ሆኖ ያየለትን ሹመት ቢሆን ዝና ወይም የሰው መውደድ አትረፍርፎ ሊሰጠው እንደሚችል ከዳዊት ህይወት መማር እንችላለን።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "የፍልስጤማውያን ጦር አዛዦች እንደወትሮው ሁሉ ለጦርነት ይወጡ ነበር፤ ዳዊትም ከቀሩት የሳኦል መኳንንት የበለጠ ድል አገኘ፣ ስሙም የታወቀ ሆነ።" 1ኛ ሳሙ 18፡30

1. 1ኛ ሳሙ 18፡1-30 በአንድነት ይነበብ። ቁ1-4ትን ስታነብ የሳኦል ልጅ ዮናታን ዳዊትን የወደደበትን ፍቅር ለመግለጽ ጸሐፊው የተጠቀመባቸውን አነጋገሮች ተናገር። ዮናታን የፍቅሩን እውነተኛነትና ከልቡ መሆኑን ሊያስገነዝበን የሚችል ግልጽ ሆነው የምታያቸው የወሰዳቸው እርምጃዎች ካሉ ተናገር።
2. ቁ5-6 ስናነብ ዳዊት በሳኦል ዘንድ ሹመትን ለማግኘት ስለበቃበት ምክንያት ይህ ክፍል ምን ይነግረናል? ዳዊት ከሳኦል ዘንድ ሹመት መቀበሉ ህዝቡ በሙሉ ደስ እንደተሰኘ እናነባለን። ለምንድነው ህዝቡ ሁሉ የሳኦል ሹማምንቶች እንኳን ሳይቀሩ በዳዊት መሾም ደስ የተሰኙት ለምንድነው ብለህ ትገምታለህ?
3. ቁ7-9 ባለው ቁጥር ላይ ስትመለከት ንጉስ ሳኦልን እጅግ በጣም ያስቆጣውና ያልተደሰተበት ነገር እንደነበረ ይነግረናል፤ ይህ ሳኦልን ያስከፋው ነገር ምን ነበረ? ሴቶቹ የዚህ ዓይነት ዘፈን ማውጣትና መዝፈናቸው ትክክለኛ ነው ብለህ ታምናለህ ወይ? ለምን? ሳኦል እስከ እድሜው መጨረሻ ቀን ድረስ ዳዊትን ሲያሳድድ እንደነበረ የታወቀ ነገር ነው፤ ለምንድነው ይህ ሴቶቹ የዘፈኑበት ቀን ወደፊት ሊሆን ላለው ነገር ወሳኝ ቀን ነበረ ማለት የምንችለው?
4. ቁ10-14 በቤተ መንግሥት ውስጥ ሳሉ ዳዊትና ሳኦል ሁለቱም ከእጃቸው የማይለዩት ሁልጊዜ ሊጠቀሙበት ዝግጁ የሆነ ነገር ምን ታያለህ? እነዚህን ቁጥሮች በምናነብበት ጊዜ፤ እግዚአብሄር ከእርሱ ጋራ የሆነ ሰው ህይወቱን ከሌሎች ሰዎች የሚለዩት ቢያንስ ሁለት ነገሮችን ማየት እንችላለን፤ እነዚህ ሁለት ነገሮች ምን ምንድናቸው?
5. ቁ15-17 ሳኦልና የእስራኤል ህዝብ ለዳዊት የነበራቸው ስሜት የተለያየ እንደነበረ ከነዚህ ቁጥሮች እንረዳለን። ሳኦል ለዳዊት የነበረው ስሜትና ህዝቡ ለዳዊት የነበራቸው ስሜት ምን ይመስል ነበረ? መዝ 19፡14ት ላይ መዝሙረኛው ዳዊት እግዚአብሄርን ሲለምን የምናየው ጸሎት፤ በዚህ ክፍል ውስጥ ሳኦል የወደቀበትና የተሸነፈበት ነገር እንደሆን የምናየው እንዴት እንደሆነ አስረዳ። እኛስ አፋችን አንድ ነገር እየተናገረ ልባችን ሌላ ነገር ያስብ ይሆን? ይህ ሲከሰትብን፤ የዳዊትን ጸሎት መጸለይ መልካም ይሆናል።
6. በቁ17-21ን ስናነብ ሳኦል ለዳዊት ልጁን ሜሮብን እንደሚድርለት ቃል ኪዳን ሲገባ እናነባለን፤ በቁ 19 ላይ ደግሞ ይህችንው ለዳዊት ቃል የገባለትን ልጅ ለሌላ ሰው ሲሰጥበት እንመለከታለን። ከዚህ ድርጊቱ ስለሳኦል ባህርይ ምን መናገር እንችላለን? ሳኦል በዚህ ክፍል ውስጥ ደስ እንደተሰኘ እናነባለን፤ የዚህ ሰው ደስታ የመነጨው ዳዊት መልካም ሚስት ሊያገኝ ነው፣ ወይም ደግሞ ልጄ ጀግናና እግዚአብሄርን የሚፈራ ሰው ልታገኝ ነው በሚል ነበረ ወይ? ካልሆነስ የደስታው ምክንያት ምን ነበረ ትላለህ?
7. ቁ22-27 በተለይም ቁ22ትን ስንመለከት በሳኦል ላይ አንድ ሌላ እግዚአብሄርን የማይስደስት ባህርይ እናይበታለን፤ ይህ ባህርይ ምንድነው ብለህ ታምናለህ? በቁ21 ላይ ሳኦል ደስ የተሰኘበትን ምክንያትና፤ በቁ26 ላይ ደግሞ ዳዊት ደስ የተሰኘበትን ምክንያት በማነጻጸር ተናገር። ያንተስ ደስታ በሰዎች ውድቀት ነው ወይስ እግዚአብሄር ለራስህ ባመቻቸልህ በረከት?
8. ቁ28-30 በተለይም በቁ30 ላይ በዳዊት ህይወት ውስጥ ስለታየው ስኬታማነት የተነገሩት ነገሮች ምን ምንድናቸው? ዳዊት ሹመትን፣ ታዋቂነትን፣ በሰው መወደድንና የመሳሰሉትን ለማግኘት ያደረገው ጥረት ታያለህ ወይ? አንተስ እነዚህንና የመሳሰሉትን ነገር ለማግኘት የምትሞክርባቸው መንገዶች ምን ምንድናቸው? ሰው አካሄዱ እግዚአብሄርን በመፍራትና እርሱን ተስፋ በማድረግ ከሆነ፤ መልካም ስም፣ ሹመት፣ ዝናና በሰው መወደድ ሁሉ ከእግዚአብሄር የሚሰጡ በረከቶች እንደሆኑ መረዳት ያስፈልጋል።

# ጥናት አስራ ስምንት 1ኛ ሳሙ 19፡1-24

የጥናት ዓላማ፡- ሳኦል ለወጥመድነት ያዘጋጃት ሚልኮል፤ እግዚአብሄር ለዳዊት የደህንነት መንገድ አድርጎ እንደተጠቀመባት፤ ጠላታችን የሆነው ሰይጣንም ለእኛ መጥፊያ አስቦ የሚያመጣቸውን ወጥመዶች አምላካችን በቸርነቱ ለደህንነታችን እንደሚቀይራቸው ለመማር።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "እናንተ እኔን ለመጉዳት አስባችሁ አድርጋችሁት ነበር፤ እግዚአብሄር ግን ዛሬ እንደሚታየው ሁሉ የብዙዎችን ህይወት ለማዳን ለበጎ ነገር አዋለው።" ዘፍ 50፡20 በተጨማሪም ሮሜ 8፡28ትን ማንበብ ይረዳል።

1. 1ኛ ሳሙ 19፡1-24 በአንድነት ይነበብ። በቁ1-3 ውስጥ ስናነብ ንጉሱ ሳኦል በዳዊት ላይ ያደረበት ጥላቻ ከምን ደርሶ ነው የምንመለከተው? እግዚአብሄር ዳዊትን ከክፉ ለመታደግ በቤተ መንግሥት ውስጥ ሰው እንዳሥቀመጠለት እናያለን፤ ይህ ዳዊትን ለማዳን እግዚአብሄር እየተጠቀመበት ያለው ሰው ማን ነው? በዚህ ሥፍራ አባት ለልጁ እያስተማረ ያለው ክፉና ጠማማ ነገር ምንድነው ትላለህ?
2. ቁ4-6ትን በማንበብ የሳኦል ልጅ ዮናታን ዳዊት እንዳይገደል ለማድረግና እርሱን ለማስመለጥ የአባቱን አስተሳሰብ ለመቀየር የሰነዘራቸው ሃሳቦች ምን ምን እንደነበሩ በመዘርዘር ተናገር። ዮናታን የአባቱን ሃሳብ ለማስቀየር ያደረገው ሙከራ ለጊዜው ምን ያህል ፍሬአማ ነበረ? ይህ ንጉስ በዳዊት ላይ ክፉ እንደማያደርግና እንደማይገደል በቁ6 ላይ በእግዚአብሄር ሥም በመማል ይናገራል፤ ስለሳኦል ህይወት ከምታውቀው ይህ ሰው መሃላውን የጠበቀ ይመስልሃል ወይ?
3. ቁ7-10 በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ስንመለከት ዳዊት ሁለት ዓይነት ጠላቶች እንደነበሩት እንመለከታለን፤ እነዚህ ሁለት ዓይነት ጠላቶች እነማን ነበሩ? ከነዚህ ሁለት ዓይነት ጠላቶች ለዳዊት አስቸጋሪ የነበረውና ለህይወቱ አደገኛ የሆነበት የትኛው ዓይነት ጠላት ነው ትላለህ? በአንተ ህይወት ወይም ደግሞ በቤተ ክርስትያን ውስጥ ስትመለከት አስቸጋሪ ሆኖ የሚገኘው ከውጭ የሚነሳ ጠላት ነው ወይስ የውስጥ ጠላት? ተወያዩበት።
4. ከዚህ ቀደም ብሎ በተመለከትናቸው ክፍሎች ውስጥ ዳዊትን ለማስገደል ይሞክር የነበረው በፍልስጤማውያን እንደነበረ እናውቃለን። በዚህ በቁ11-13 ላይ ስናነብ ንጉሱ ሳኦል ዳዊትን ለመግደል መሳሪያ አድርጎ ሊጠቀም ሲሞክር የምናገኘው እነማንን ነው? በነዚሁ ቁጥሮች ውስጥ ደግሞ እግዚአብሄር ለዳዊት የመዳኛ መንገድ አድርጎ ሲጠቀም የምናየው ማንን ነው? ሳኦል የራሱ ሃጥያትን ማድረግ አንሶት ሌሎችን የሃጥያቱ ተካፋይ ማድረጉ ምን ያመለክተናል?
5. ቁ14-17 ከዚህ ቀደም ዳዊት በ1ኛ ሳሙ 18፡17 ላይ ዳዊትን ስለመግደል አስመልክቶ ሲናገር ያነበብነው ነገር ምን ነበረ? ዛሬ ባነበብነው ክፍል ውስጥ ደግሞ ቀድሞ የነበረውን አመለካከት እንደለወጠ እንረዳለን። ዳዊትን መግደል አስመልክቶ ይህ ክፍል በ1ኛ ሳሙ 18፡17 ላይ ካለው ክፍል የሚለይበትን ነገር ተናገር። እስካሁን ካጠናነው፤ ሳኦል ዳዊት እንዲሞት ስንት መንገድ ሞከሯል?
6. ቁ18-20ን ስናነብ ዳዊት ሳኦል ሊገድለው ሲሞክር ያደረገው ነገር ምን ነበረ? ያንን የሚያህል ከነሙሉ ትጥቁ የመጣበትን የፍልስጤም ጀግና በባዶ እጁ ገጥሞ ያሸነፈው ጀግና ከሳኦል ፊት መሸሹ ለምንድነው ብለህ ታምናለህ? እግዚአብሄር የሰጠንን እውቀትም ሆነ ብልህነት በእግዚአብሄር ህዝብ ላይ እንድንጠቀምበት ሳይሆን በጠላታችን ላይ እንድናውለው ነው።
7. ቁ21-24 "ሳሙኤልና ዳዊት የት ናቸው? ሲል ጠየቀ።" ይህንን ስናነብ ሳኦል ለሳሙኤል ስለነበረው አመለካከት ምን መረዳት እንችላለን? ሌሎቹ ሁሉ ትንቢት ሲናገሩ እርቃናቸውን ሆነው መሆኑን የሚናገር ነገር የለም፤ ሳኦል ግን ለረጅም ጊዜ ማለተም ቀኑንና ሌሊቱን ሙሉ ራቁቱን እንደነበረ እናነባለን። ይህ ሳኦል የነበረበት ሁኔታ ምን ሊናገረን የሚችለው ነገር ይኖራል ትላለህ?
8. 1ኛ ሳሙ 18፡20-21 እና 1ኛ ሳሙ 19፡11-12 ላይ የሰፈሩትን ሃሳቦች ስንመለከት ሳኦል ሚልኮልን ለዳዊት በሚስትነት የሰጠበት ምክንያት ምን ነበረ? እግዚአብሄር ለወጥመድነት የተሰጠችውን ሴት በምን መንገድ ሲጠቀምባት ነው የምናየው? ከዚህ የእግዚአብሄር አሰራር ለህይወትታችን የሚያስተምረን ነገር ምንድነው? ጠላት ህይወትህን ለማጥፋት የሚያዘጋጀውን ወጥመዱን አምላክህ ለደህንነትህ መንገድ አድርጎ ሊጠቀምበት እንደሚችል ማስተዋል ያስፈልግሃል።

# ጥናት አስራ ዘጠኝ 1ኛ ሳሙ 20፡1-42

የጥናት ዓላማ፡- እግዚአብሄር ዙፋን ያሰበለትን ሰው ሳዖል ሞት ቢያስብለትም እንኳን የእግዚአብሄር ሃሳብ በልጦ ዙፋን ላይ እንደተቀመጠ ሁሉ፤ እኛም እግዚአብሄር ያሰበልንና ያየልን እንጂ ሰዎች ያሚረቱብንና ያሰቡልን ነገር እንደማይወርሰን ለመማር።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "የእሴይ ልጅ በምድር ላይ በህይወት እስካለ ድረስ አንተም ሆንህ መንግሥትህ አትጸኑም። መሞት ስለሚገባው፣ ሰው ላክና አስመጣልኝ።" 1ኛ ሳሙ 20፡31

1. 1ኛ ሳሙ 20፡1-42 በአንድነት ይነበብ። ቁ1-9 የሳዖል ዳዊትን ለመግደል ሙከራ እውነተኛ ነገር እንደሆነ ዳዊት ለጓደኛው ለዮናታን በተጨባጭ አንድ ጊዜ ለመጨረሻ ለማረጋገጥ የተጠቀመበት መንገድ ምን ነበረ? ዳዊት "በእኔና በሞት መካከል አንድ እርምጃ ብቻ ቀርቷል" ብሎ ሲናገር ምን ማለት ፈልጎ ይመስልሃል?
2. ቁ10-15 ላይ ስታነብ ቢያንስ አምስት ጊዜ ያህል የተጠቀሰ አንድ ቃል አለ፤ ይህ ቃል ምን እንደሆነ ተናገር። ከዚህ ሁኔታ ስንመለከት፤ የዳዊትና የዮናታን ግንኙነት መሰረት ያደረገው በምን ላይ እንደሆነ ነው የምንረዳው? ቁ13ት ላይ ከዮናታን አነጋገር ስንመለከት፤ አባቱ ከእግዚአብሄር ጋራ ስለነበረው ግንኙነት ሊጠቁመን የሚችለው አንድ እውነት ምንድነው ትላለህ?
3. በቁ14-15 ከምናነበው ሃሳብ በመነሳት ዮናታን ስለዳዊት የተረዳው ነገር እንዳለ ግልጽ ነው፤ ከንግግሩ በመነሳት ይህ ዮናታን ስለዳዊት ያወቀ ወይም የተረዳ የሚመስለው ነገር ምን ነበረ ብለህ ትገምታለህ? "የዳዊትን ጠላቶች እግዚአብሄር ይፋረዳቸው" በማለት ዮናታን ሲናገር እግዚአብሄር እንዲፋረድ ከሚላቸው መሃል ማን ይገኝበታል?
4. ዮናታንና ዳዊት በቁ18-23 ላይ የእግዚአብሄርን ፈቃድ ለመለየት የተጠቀሙበት መንገድ ምን ነበረ? በዚህ ክፍል ውስጥ እነዚህ ሁለት ሰዎች የቃል ኪዳን ልውውጥ ሲያደርጉ ለተለዋወጡት ሃሳቦች ሁሉ በምስክርነት ሲጠራ የምናየው ማንን ነው? አንተስ ለሰዎች እሆናለሁ ወይም ደግሞ አደርጋለሁ በማለት የምትገባውን ቃል ኪዳን በመሃላችሁ ሆኖ የሚሰማ ምስክር እንዳለ ታውቃለህ?
5. ቁ24-29 ይነበብ። በቁ27 ላይ ስንመለከት ሳዖል ይህንን ያህል ጊዜ ከዳዊት ጋራ እየኖረና በፊቱ እያገለገለው ዳዊትን ለመጥራት የሚጠቀመው "የእሴይ ልጅ" በማለት ነበረ። ሳዖል በስሙ የማይጠራውና በዚህ ዓይነት አጠራር የሚጠራው ለምንድነው ብለህ ታስባለህ?
6. ቁ30-31 ዳዊት በመቀመጫው ላይ እንደሌለና ዮናታን ፈቅዶለት ወደ ቤተሰቦቹ እንደሄደ ሲነገረው የሳዖል ምላሽ ምን ይመስል ነበረ? ንጉስ ሳዖል የልጁን የዮናታንን እናት ማለትም የገዛ ሚስቱን ምን በሚል አጠራር ሲጠራት ነው የምናነበው? በግብዣው ላይ የተቀመጡ ብዙ ትላልቅ መኳንንቶችና መሳፍንቶች፣ አለቆችም ሁሉ እንደሚኖሩ የታወቀ ነው፤ ሳዖል የገዛ ልጁንና ሚስቱን በዚህ አይነት አነጋገር ሲናገር በግብዣው ላይ የነበሩት ስለ ንጉሳቸው የሚኖራቸው አስተሳሰብ ምን ይመስልሃል?
7. በቁ30 ላይ ሳዖል በተቆጣበት ቁጣና፤ በቁ34 ላይ ዮናታን በተቆጣበት ቁጣ መሃል ልዩነት ይታይሃል ወይ? ልዩነት የሚታይህ ከሆነ ይህ ልዩነት ምን እንደሆነ ተናገር። በቁ41 ላይ ዳዊትና ዮናታን ላመለያየት የስንብት ነገር ሲያደርጉና እንደተሳሳሙና እንደተላቀሱና ዳዊት የበለጠ እንዳለቀሰ እናነባለን። ለምን ይመስልሃል ዳዊት ይበልጥ ያለቀሰው?
8. እግዚአብሄር በ1ኛ ሳሙ 16፡12-13 ላይ ህዝቡን እስራኤልን ይገዛል ብሎ የተናገረለትን ሰው፤ ቁ31ድን መለስ ብለን ስናይ ሳዖል ግን ሳዖል መሞት ይገባዋል በማለት ሲናገር እናነባለን። የዳዊትን ህይወት አቅጣጫ አስመልክቶ ሳዖልና እግዚአብሄር የተለያየ ግብ ነበራቸው። በዳዊት ህይወት ተፈጽሞ የምናየው የሳዖል ሃሳብ ነው ወይስ የእግዚአብሄር? በእኛም ህይወት ሰዎች ምንም ያህል ሊያጠፉንና ሊጥሉን ቢሞክሩ፤ መጨረሻችንን የሚወስን እግዚአብሄር እንጂ ማንም እንዳይደለ ልንረዳ ያስፈልገናል።

# <u>ጥናት ሃያ 1ኛ ሳሙ 21፡1-15</u>

የጥናት ዓላማ፡- በዳዊት እጅ የገባው የጎልያድ ሰይፍ እግዚአብሄር በፈተና ሰዓት ማዳን የሚችል አምላክ እንደሆነና ዛሬም በመዋሸት መዳን እንዳይሞከር መታሰቢያ ሊሆን እንደሚችል ሁሉ፤ በእኛም ህይወት ትናንት የረዳን እግዚአብሄር ዛሬም ሊረዳን እንደሚችልና ካለንበት ሁኔታ ውስጥ ለመውጣት የሃጥያትን መንገድ መከተል እንደሚይኖርብን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- “ካህኑም፤ በኤላ ሸለቆ አንተ የገደልከው የፍልስጤማዊው የጎልያድ ሰይፍ እዚህ አለ፤ ከኤፉዱ በስተኋላ በጨርቅ ተጠቅልሏል ከፈለግህ ወሰደው።” 1ኛ ሳሙ 21፡9

1. 1ኛ ሳሙ 21፡1-15 በአንድነት ይነበብ። በቁ1-2 ላይ ዳዊትና አቢሜሌክ ያደረጉትን ውይይት ስንመለከት፤ የካህኑ የመጀመሪያ ጥያቄው ምን ነበረ? ለምን ይመስልሃል ይህንን ዓይነት ጥያቄ ለዳዊት መቅረብ አስፈላጊ ሆኖ የሚገኘው? የዳዊትን መልስ ስታነብ ምን ያህል እውነተኛነት ታይበታለህ?
2. በቁ2-3 ላይ “ስለ ላኩህ ነገርና ስለሰጠሁህ መመሪያ ማንም ሰው ምንም ነገር አይወቅ ብሎ አዞኛል።” በማለት ዳዊት ሲናገር፤ ካህኑ አቢሜሌክ ቀጥሎ ለመጠየቅ ለሚያስበው ጥያቄዎች አስመልክቶ ሊያስተላልፍ የፈለገው መልዕክት ምን ይመስልሃል? ከንጉስ ገበታ ላይ ይመገብ የነበረው ይህ ዳዊት በዚህ ቦታ ላይ በምን ዓይነት ሁኔታ ላይ ሆኖ ነው የምናገኘው?
3. ዳዊት እየደጋገመ ሌሎች ሰዎችም ከእርሱ ጋራ እንዳሉ ነገር ግን አብተውት ካህኑ ወደሚገኝበት ቦታ እንዳልመጡ አድርጎ ይናገራል፤ የሌሎች ሰዎች ከእርሱ ጋራ መኖር እውነተኛ ነገር ነበረ ወይስ ዳዊት ታሪኩን አሳማኝ እንዲሆን የተጠቀመበት ነገር ነበረ? ቁ4 ላይ ካህኑ “ሰው ሁሉ የሚበላው እንጀራ የለኝም” ማለቱ ምን ለማለት ፈልጎ ነው?
4. በቁ7 ላይ ጸሐፊው ኤዶማዊው ዶይቅ በዚያ እንደነበረ እንጂ ሌላ ተጨማሪ መረጃ የጻፈው ነገር የለም። ለምን ይመስልሃል የዚህን ሰው በዚያ መገኘት ጠቅሶ ማለፍ የፈለገው? ዳዊት እርሱና ከእርሱ ጋራ የነበሩት ሰዎች የሚበሉትን እንጀራ ከያዘ በኋላ የሚቀጥለው ሙከራው ምን ለማግኘት ነበረ?
5. ቁ2-3ትና ቁ9 ላይ ያሉትን ሃሳቦች ስንመለከት ዳዊት እንጀራውንና የጦር መሳሪያውን ለማግኘት የተጠቀመባቸው መንገዶች በምን መንገድ ነው የሚመሳሰሉት? ሳዖል ሊቀበል ያልቻለው ነገር ግን ዳዊት ሸሽቶ በሄደባት ምድር ያሉት አህዛብ ስለዳዊት የተቀበሉት ወይም የተናገሩት አንድ እውነት ምን ነበረ?
6. ቁ10ርን ስናነብ ዳዊት ሳዖል ሲያሳድደው የእግዚአብሄር ህዝብ ከሚገኝበት አካባቢ ሸሽቶ የሄደው ወደየት ነበረ? በቁ10 ላይ ዳዊት ተነስቶ እንደሄደ የተነገረላት የጌት ከተማ 1ኛ ሳሙ 17፡4ትን ስንመለከት ይህች ከተማ ከዳዊት ህይወት ጋራ የሚያያዝበት ምን ነገር ትመለከታለህ?
7. ቁ12-15 ላይ ስናነብ ዳዊትን ወደ ተጨማሪ ውሸትና ራሱን እንደ እብድ አድርጎ እንዲቀይር ያደረገው ነገር ምን ነበረ?
8. በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስንመለከት ዳዊት ከነበረበት ሁኔታ ውስጥ ለመውጣት በተደጋጋሚ ሲጠቀምበት የምናየው ታክቲክ ምንድነው? ዳዊት መለስ ብሎ ማስተዋል ቢችል፤ በእጁ የያዘው የጎልያድ ሰይፍ በምን ዓይነት ነው በውሸት ማምለጥ እየሞከረ ያለውን መንገዱን ማስቀየር የሚችለው? ዛሬ ካለህበት ሁኔታ ውስጥ ለመውጣት የሃጥያትን መንገድ ለመጠቀም ስታስብ፤ ትናንት እግዚአብሄር ማምለጥ ከማትችለው ሁኔታ ውስጥ እንዳስመለጠህ መለስ ብለህ ማሰብ ይኖርብሃል።

# ጥናት ሃያ አንድ ፲ኛ ሳሙ 22፡1-23

የጥናት ዓላማ፡- ዳዊት ሐጥያቱን አምኖ ጥፋተኛነቱን ሙሉ በሙሉ መቀበሉ በእግዚአብሄር ዘንድ እንደልቤ ከመባል እንዳልከለከለው ሁሉ፤ እኛም ያጠፋነውን ጥፋት ወይም ሃጥያት አምነን መቀበላችን በእግዚአብሄር ዘንድ ክብርን እንጂ ውርደትን እንደማያመጣብን ለመማር።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- “ለመላው የአባትህ ቤተሰብ እልቂት ተጠያቂው እኔ ነኝ።” ፲ኛ ሳሙ 22፡22

1. ፲ኛ ሳሙ 22፡1-23 በአንድነት ይነበብ። ቁ1-2 ላይ እግዚአብሄር ዳዊት እግዚአብሄር ዳዊትን በሁለት መንገዶች ባረከው ብለን ብንናገር ባርኮቶቹ ምንና ምን እንደሆኑ ተናገር። ዳዊት እስራኤልን ሁሉ መምራት እንዲችል እግዚአብሄር ሊያለማምደው የፈለገው ምን ዓይነት ሰዎችን በመስጠት ነበረ?
2. ቁ3-4 ዳዊት እግዚአብሄር ለንጉስነት እንደቀባው ያውቃል፤ ለምን ይመስልሃል በዚህ ቦታ ሲናገር ልክ እግዚአብሄር በህይወቱ ሊያደርግ ያለውን ነገር እንደማያውቅ አይነት ሰው ሆኖ የሚናገረው? ዳዊት በዚህ ሽሽትና መከራ ውስጥ ሆኖ እያለ፤ በዚህ ክፍል ከራሱ ሁኔታ አልፎ እያሰበ ያለው ለማን ነው?
3. ቁ5 ላይ ስናነብ እግዚአብሄር በነብዩ ጋድ በኩል ከተደላደለበት ዓምባ ውስጥ ወጥቶ ወደየት እንዲሄድ ነው የተናገረው? በነብዩ በኩል ከእግዚአብሄር የመጣለትን መልዕክት ሰምቶ ዳዊት የወሰደው እርምጃ ምን ነበረ? ዳዊት ይህንን የእግዚአብሄር ቃል ላለመታዘዝ መስጠት የሚችለው ምን ምክንያት ሊኖረው ይችል ነበረ ትላለህ? በብቸኝነት ጊዜም ጌታ መናገሩን አለማቆሙ ግሩም ነው! ሆኖ እግዚአብሄር ስሜት የማይሰጥ ትዕዛዝ ሲሰጥህ ለመታዘዝ ምን ያህል ዝግጁ ነህ?
4. ቁ6-8 “ሳዖልም...ጦሩን በእጁ ይዞ ተቀምጦ ነበር” ሳዖል ጦሩን ምንም ባላደረጉት በዳዊትና በልጁ በዮናታን ላይ እንኳን ለመግደል እንደወረወረው እናውቃለን፤ ታዲያ በዚህን ጊዜ ሳዖል ይህንን ንግግር ሲያደርግ በሳዖል ሹማምንት አዕምሮ ውስጥ ሊያልፍ የሚችለው ነገር ምን ይሆናል ብለህ ትገምታለህ? ዶይቅ በቁ9-10 ላይ የካህኑ የአቢሜሌክ ጥፋት አድርጎ የዘረዘራቸው ሶስት ነገሮች ምን ምን ነበሩ?
5. ቁ11-15ትን ስናይ ሳዖል ስለዳዊት እየተናገረ ያለው ቢያንስ ሁለት እውነት ያልሆኑ ነገሮችን እናያለን፤ እነዚህ ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? ካህኑ አቢሜሌክ ደግሞ ስለዳዊት የሚናገራቸው ቢያንስ አምስት የሆኑ እውነቶች በዚሁ ክፍል ውስጥ ተዘርዝረው ይገኛሉ፤ እነዚህ ምን ምን እንደሆኑ ተናገር። እኛም ወንድሞቻችንን እያሳደድን፤ በሰዎች ፊት ግን እንደተበዳይ ሆነህ ራሳችንን ለማቅረብ ስንዋሽ እንዳንገኝ ልንጠነቀቅ ያስፈልገናል።
6. ዳዊት ስለ ኤዶማዊው ዶይቅ በቁ22 ላይ ከሚናገረው አነጋገር ስትመለከት፤ ስለዚህ ዶይቅ ስለተባለው ሰው ምን መረዳት ትችላለህ?
7. በ፲ኛ ሳሙ 21፡7 ላይ በእግዚአብሄር ቤተ መቅደስ ውስጥ የምናየው ዶይቅ በ፲ኛ ሳሙ 22፡18-19 ላይ ሌሎቹ የሳዖል ሹማምንት አንገድልም ያሏቸውን የእግዚአብሄር ካህናት ዶይቅ ሰይፉን መዞ ሰማንያ አምስቱን እንደገደለ እናነባለን። ዶይቅ  የእግዚአብሄር ቤት አዘውታሪ መሆኑና ተግባሩ ሲታይ ደግሞ ሌላ የመሆኑን ነገር፤ አሁን እኛ ካለንበት ዘመን ጋራ በማነጻጸር ምን ማለት ሊሆን እንደሚችል ለማስረዳት ሞክር።
8. በቁ15 ላይ “ንጉሥ...ማንንም ጥፋተኛ አያድርግ” በማለት ካህኑ አብያታር ለሳዖል ሲናገር እናያለን፤ በዚህ በቁ22 ላይ ደግሞ ዳዊት “ለመላው የአባትህ ቤተሰብ እልቂት ተጠያቂው እኔ ነኝ።” በማለት ሲናገር እናነባለን። እነዚህ ሁኔታዎች ስለሳዖልና ስለዳዊት ባህርይ ምን ይናገራሉ? አንተስ ለገባህበት ሁኔታ ወይም ላደረከው ነገር ሰዎች ላይ ማሳበብ ይቀናሃል ወይ? ለጥፋታችን ሙሉ ተጠያቂነት የምንወስድ ሰዎች እንጂ በሌሎች ላይ በማሳበብ ልምድ መኖር ትክክል ነገር አይደለም።

# ጥናት ሃያ ሁለት 1ኛ ሳሙ 23፡1-29

የጥናት ዓላማ፡- ዳዊትና አብረው የነበሩትን ሰዎች በአጣብቂኝ ሁኔታ ውስጥ ሳሉ እግዚአብሄር ራሱ መፍትሄ አምጥቶ እንደገላገላቸው ሁሉ፤ እኛም መውጣት የማንችልበት አጣብቂኝ ሁኔታ ውስጥ ገብተን ምንም ማድረግ እንደሚገባን ግራ ሲገባን እርሱ ብቻውን መፍትሄ ሊሆነን እንደሚችል ለመማር።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- “ሳዖልና ወታደሮቹ ዳዊትንና ሰዎቹን ከበው ለመያዝ ተቃርበው ሳሉ፤ አንድ መልዕክተኛ ወደ ሳዖል መጥቶ ፍልስጤማውያን አገሩን ወረውታልና ቶሎ ድረስ አለው።” 1ኛ ሳሙ 23፡26-27

1. 1ኛ ሳሙ 23፡1-29 በአንድነት ይነበብ። በቁ1-4 ላይ ፍልስጤማውያን ቅዒላን እየዘረፉ እንደሆነ ዳዊት ሲሰማ መጀመሪያ የወሰደው እርምጃ ምን ነበረ? እግዚአብሄር ዳዊት ለጠየቀው ጥያቄ የሰጠው መልስ በህዝቡ ዘንድ የነበረው ተቀባይነት ምን ዓይነት ነበረ? ከዳዊት ጋራ የነበሩት ሰዎች ላነሱት ጥያቄ የዳዊት ምላሽ ምን እንደነበረ ትናገር።
2. ቁ4-6ትን ስናነብ ዳዊት ለሁለተኛ ጊዜ ሄዶ ፍልስጤማውያንን መምታት እንደሚችል ከእግዚአብሄር ማረጋገጫን ካገኘ በኋላ ያደረገው ነገር ምን ነበረ? “...ዳዊት የቅዒላን ህዝብ ታደገ” ቁ5 በዚህን ጊዜ ንጉስ የነበረው ሳዖል ሆኖ እያለ የቅዒላን ሰዎች ለመታደግ መሄድ ስለዳዊት ባህርይ ምን ይነግረናል? ዳዊት ምንም እንኳን አንድ ጊዜ እግዚአብሄርን የጠየቀ ቢሆንም፤ ከእርሱ ጋራ የነበረው ህዝብ እንደፈራና ከእርሱ ጋራ ለመውጣት ሙሉ ለሙሉ አለመስማማቱን ሲያውቅ ዳግመኛ ወደ እግዚአብሄርን ለመጠየው መሄዱ የሚያስተምርህ ነገር ካለ ለወገኖች ተናገር።
3. የአቢሜሌክ ልጅ አብያታር ሳዖል የአባቱን ቤተሰብ ሁሉና የእግዚአብሄርን ካህናት ሁሉ በገደለ ጊዜ ወደ ዳዊት ሲሸሽ ይዞ የሸሸው አንድ ነገር ምን ነበረ? ቁ7-8ትን ስናነብ ለምንድነው ሳዖል ዳዊትን በእጁ እንደገባለት የቆጠረው? ዳዊት በቁ2 እና ሳዖል ደግሞ በቁ7 ላይ እግዚአብሄርን በጉዳያቸው ውስጥ ሲያስገቡት እንመለከታለን። ሁለቱ ሰዎች የእግዚአብሄርን ከእነርሱ ጋራ ለማቆም የተጠቀሙበት መንገድ ምን እንደሆነ፤ የማንኛቸው መንገድ ደግሞ ትክክለኛ ነው ብለህ እንደምታስብ ተናገር።
4. ቁ9-12ትን በማንበብ ዳዊት ለእግዚአብሄር ያቀረባቸው ሁለት ጥያቄዎች ምንና ምን እንደሆኑና፤ እግዚአብሄር ለዳዊት ጥያቄዎች የሰጣቸው ምላሾች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር። የቅዒላ ሰዎችን ነጻ ለማውጣት ዳዊት የራሱንና በሰዎቹ ነፍስ ቆርጦ ያዳናቸውን ሰው ሳዖል ሲመጣ አሳልፈው ለእርሱ እንደሚሰጡት እግዚአብሄር ሲያረጋግጥለት በቁ12 ላይ እናነባለን፤ የእነዚህ ሰዎች ሁኔታ ስለሰው ልጅ ባህርይ የሚነግረን እውነት ምንድነው?
5. ቁ13-14 ላይ ስንመለከት ዳዊት በጠላትነት ከሚያሳድደው በሳዖል እጅ እንዳይወድቅ ለህይወቱ መጠንቀቅ የነበረበት መቼ መቼ ነበረ? በዚህ ሁሉ ውስጥ የእግዚአብሄር አስተዋጽዖ ምን ሆኖ ነው የምናየው? ይህንን እውነት ከክርስትና ህይወታችን ጋራ በማገናዘብ ለእኛ ህይወት ሊናገር የሚችለውን እውነት ለወገኖች ተናገር።
6. የሳዖል ልጅ ዮናታን ወደ ዳዊት መጥቶ በቁ15-17 ላይ ሲያደርግ የምንመለከተው ነገር ምንድነው? በተለይ ዮናታን የተጠቀመበት የዚህ ዓይነት የማበረታቻ መንገድ ሌሎች ሰዎች ከሚጠቀሙበት የማበረታቻ መንገድ በይበልጥ ለዳዊት ውጤታማ ሊሆን የሚችለው ለምን ይመስልሃል? የአንተንስ መከራ ለማስረሳትና ካለህበት አዘቅት ውስጥ ለማውጣት ሰዎች የእግዚአብሄርን ስም ይዘው ወይስ ሌላ የተሻለ የሚስማማህ መንገድ አልህ?
7. ቁ18ትን ስናይ “ዮናታን ወደ ቤቱ ሄደ፤ ዳዊት ግን እዚያው ሖሬሽ ተቀመጠ” በማለት ይነግረናል። የዮናታን መምጣት ዳዊት ከነበረበት ችግር ውስጥ አውጥቶት እናያለን ወይ? ታዲያ ዳዊትን ከነበረበት ሁኔታ ውስጥ ማውጣት ካልቻለ የዮናታን ያንን ያህል ርቀትና ምድረበዳውን ሁሉ ተጉዞ መምጣቱ ምን ትርጉም አለው ትላለህ? እኛም የሰዎችን ችግር መፍታት ሳይሆን ፍቅራችንን ማሳየትና፤ ሰዎች በእግዚአብሄር ላይ በእምነታቸው እንዲበረቱ ማገዝ ነው።
8. ቁ19-23ትን በማንበብ ሳዖል ዳዊትን ምን ዓይነት ሰው አድርጎ ነው ሲናገር የምንሰማው? ዳዊት እውነት ሳዖል እንደሚያስበው ከእርሱ ወጥመድ እያመለጠ ያለው በተንኮሉ ነው ወይስ ሌላ እርሱ የማያውቀው ምስጢር አለ?
9. የዳዊት ከጠላቱ የማምለጥ ምክንያት እጅግ ተንኮለኛ ከመሆኑ የተነሳ እንዳልሆነ የሚያረጋግጥልንን በቁ25-29 ውስጥ የትኛው ሃሳብ እንደሆነ በዝርዝር አስረዳ። ጠላትህ በቃ ያዘኝ ስትል እግዚአብሄር በአስገራሚ መንገድ ያስመለጠህን ጊዜ ታስታውሳለህ? በቃ አለቀልኝ በምንልባቸው ሁኔታዎች ውስጥ እያለን፤ እግዚአብሄር ልዩ የሆነ የራሱን መንገድ ተጠቅሞ ከአጣብቂኝ ሁኔታችን ውስጥ ሊያወጣን እንደሚችል እርሱን መተማመን ይኖርብናል።

## ጥናት ሃያ ሶስት 1ኛ ሳሙ 24፡1-22

የጥናት ዓላማ፡- እውነቱ ምን እንደሆነ ልባችን እያወቀው፤ እግዚአብሄር የናቃቸው አንዳንድ ሳዖሎች ሊያጠፏቸው በተነሱት የእግዚአብሄርን ቅዱሳን ላይ፤ እኛም ተጨምረን እጃችንን በማንሳት ለማሳደድ መነሳታችን እግዚአብሄር አምላክ የሚጸየፈውና ቆይቶ እኛንም የሚያጠፋን ነገር ሊሆን እንደሚችል እንደሆነ ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- “ስለዚህ ሳዖል ከመላው እስራኤል የተመረጡ ሶስት ሺህ ሰዎችን ይዞ ዳዊትንና ሰዎቹን ለመፈለግ፤ የሜዳ ፍየሎች ዓለት፤ ወደተባለው ቦታ አቅራቢያ ሄደ።” 1ኛ ሳሙ 24፡2

1. 1ኛ ሳሙ 24፡1-22 በአንድነት ይነበብ። ከ1-4 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ ስንመለከት፤ የዳዊት ሰዎች ሳዖል በግላጭ ሲገኝ ለእነርሱ ወዲያው የታያቸውና ለመሪያቸው ለዳዊት የሰጡት ምክር ምን የሚል ነበረ? የእነዚህ ሰዎች ምክር በምን ላይ የተመሰረተ ነበረ? ሰዎችን የእግዚአብሄርን ቃል ያለቦታው በመጥቀስ ለሃጥያት ማመቻቸት እንደሚቻል ታያለህ?
2. ቁ4-7 ላይ እግዚአብሄር ለዳዊት የተናገረውን ቃል የሚፈጽምበትን ጊዜ አስመልክቶ፤ ከእርሱ ጋራ በነበሩት ሰዎችና በራሱ በዳዊት መሃል ምን ልዩነት ታስተውላለህ? እንደዚህ በሰፊው የተራራቁና ሊገኛኙ የማይችሉ ሁለት ዓይነት አመለካከቶች በአንድ ነገር ላይ በምን ምክንያት ሊከሰት ቻለ ብለህ ታምናለህ?
3. ቁ4 ላይ “የዳዊት ሰዎችም ዳዊትን… አሉት” ቁ9 ላይ ደግሞ “ዳዊትም ሳዖልን እንዲህ አለው፤ ሰዎች… ሲሉ ለምን ትሰማቸዋለህ?” የሚሉ ሁለት ሃሳቦችን እናገኛለን። ከነዚህ አነጋገሮች ከአሳዳጁና ከሚሳደደው ሰው ሌላ በዚህ ፍጭት መሃል እነማንን ታያለህ? በነዚህ ሁለት ሰዎች መሃል ገብተው ለሚፈተፍቱት ሰዎች የሳዖልና የዳዊት ምላሽ ይመሳሰላል ብለህ ታምናለህ ወይ? አይደለም የምትል ከሆነ ደግሞ ልዩነቱ ምን ላይ እንደሆነ አስረዳ።
4. ዳዊት ሳዖልን እንዳይገድል በእግዚአብሄር ቃል ራሱን እንደገዛ ቁ6-7ት ላይ ተመልክተናል። ዳዊት ሳዖልን እንዳይገድለውና ሁኔታውን ተጠቅሞ ሰዎቹ እንደነገሩት እንዳያደርግበት ተጨማሪ ምክንያት ስለሆነው ነገር ቁ10 የሚነግረን ምንድነው? ቁ11-13ትን ስናነብ ዳዊት ሁለት ነገሮችን በእግዚአብሄር እጅ አሳልፎ ሲሰጥ እንመለከታለን፤ እነዚህ ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? አንተስ በህይወትህ እነዚህን ሁለት ነገሮች በእግዚአብሄር እጅ አሳልፈህ መስጠትን ምን ያህል ተምረሃል?
5. በቁ14 እና በቁ15 ዳዊት በዚህ ባለበት አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እግዚአብሄርን ሶስት ዓይነት ነገሮች ሊሆንለት እንደሚችል የተረዳ ይመስላል። እነዚህ ሶስት ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር።
6. “ክፉ ሳደርግብህ በጎ መልሰህልኛል፤ አንተ ከእኔ ይልቅ ጻድቅ ነህ።” በማለት ሳዖል ስለዳዊት በቁ17 ላይ የተናገረውን ንግግር ስንመለከት፤ ይህንን በመፈጸሙ ዳዊት በህይወቱ በተግባር ላይ አዋለ ማለት የምትለው ከእግዚአብሄር ቃል ውስጥ ትዝ የሚልህና የምታስታውሰው ጥቅስ ካለ ለወገኖች ተናገር?
7. በቁ18-22 መሰረት፤ ንጉስ ሳዖል በጠላቱ በዳዊት እጅ ላይ ወድቆ መገኘቱን እንደማን ሥራ አድርጎ ነው የተቀበለው? ዳዊት እግዚአብሄርን በመፍራትና በጽድቅ ህይወት በመመላለሱ ምክንያት በሳዖል አመለካከት ላይ ያስከተለውን በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የተናገራቸውን ነገሮች ሁሉ በመዘርዘር ተናገር።
8. ቁ2ትን መለስ ብለን ስንመለከት፤ ሳዖል ዳዊትን ለማሳደድና ለመግደል እንዲረዱት የሰበሰባቸው ሰዎች ከየት የተውጣጡ ነበሩ? ዳዊት በእስራኤል ሁሉ ዘንድ የተወደደ እንደነበረ፣ ምንም ዓይነት ጥፋት እንዳላጠፋና፣ ሳዖልን ለማበሳጨት እርሱ ያደረገው ነገር እንደሌለ የታወቀ ሆኖ እያለ፤ ለምን ይመስልሃል ከእነዚህ ሶስት ሺህ ሰዎች አንዳቸውም እንኳን ለእውነት ለመቆም ያልቆረጡት? አንተስ እውነቱ ምን እንደሆነ እያወቅህ የታዘዝከውን ሳትጠይቅ ታደርግ ይሆን? እውነትን እያወቅን ሌሎችን ደስ ለማሰኘትም ሆነ ለእነርሱ ያለንን ታማኝነት ለማረጋገጥ ሌሎችን ለማሳደድ መነሳት ጌታ የማየወደው ነገር ነው።

# ጥናት ሃያ አራት 1ኛ ሳሙ 25፡1-44

የጥናት ዓላማ፡- እግዚአብሄር ናባልን በአስቸኳይ መበቀሉና፣ ሳዖልን ለመበቀል ደግሞ ዳዊት የሚያልፍበት ሁኔታ እስኪመረው ድረስ ረጅም ዓመታት መውሰዱ፤ እግዚአብሄር ቅድሚያ የሚሰጠው እኛን ፈጥኖ ከመከራችን ማላቀቅ ሳይሆን፤ የእኛ ህይወት ለንጉስ ልጅነት የሚያበቃ፤ ማለትም የኢየሱስን መልክ እስክንመስልለት ድረስ መስራትና መለወጥ መሆኑን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- “አሥር ቀን ያህል ካለፈ በኋላ እግዚአብሄር ናባልን ቀሰፈው፣ እርሱም ሞተ” 1ኛ ሳሙ 25፡38 “ሳዖል ከቀድሞው ይልቅ ፈራው፣ እስከ እድሜውም ፍጻሜ ድረስ ጠላቱ ሆነ” 1ኛ ሳሙ 18፡29

1. 1ኛ ሳሙ 25፡1-44 በአንድነት ይነበብ። ቁ1-3 ስናነብ ስለ ናባል የተነገሩን ነገሮች ምን ምንድናቸው? እነዚህን ባልና ሚስት ስንመለከት በሁለቱ መሃል ግልጽ የሆነ ልዩነትን እንመለከታለን፤ ይህ ግልጽ ሆኖ የሚታየው ልዩነት ምን እንደሆነ ተናገር። በገንዘብ ባለጠጋ ሆኖ በባህርይ ደሃ ከመሆን እግዚአብሄር ይጠብቀን!
2. ዳዊት በቁ6 ላይ ለናባል የሚመኝለት ነገሮች ምን ምንድናቸው? ዳዊት የዚህን ሰው ትክክለኛ ማንነት ካወቀና ከተረዳ በኋላ ይህ ምኞት እንደተጠበቀ ሆኖ የቆየ ይመስልሃል ወይ? አስረዳ። ቁ10-11ድን ስንመለከት ናባል ስለዳዊት “ከየት እንደመጡ ለማይታወቁ ሰዎች…” በማለት ሲናገር እናነባለን። ዳዊት ጎልያድን በመግደል እስራኤልን ሁሉ ከባርነት ያዳነ ሰው ሆኖ እያለ፤ ናባል ይህንን ስለሚያውቅ ነው ወይስ ለምንድነው የዚህ ዓይነቱን ንግግር የሚናገረው ብለህ ታምናለህ?
3. በዚህ ክፍል ውስጥ ስለናባል ብልግና የተረዱና ያወቁ ሰዎች እነማን እንደሆኑ በመዘርዘር ተናገር። ቁ14-17 የአቢግያ አገልጋዮችን በመወከል ስለዳዊትና ከእርሱ ጋራ ስለነበሩት ሰዎች የሰጠው ምስክርነት ምን የሚል ነበረ? ቁ18-19ን ስታነብ፤ አብግያ የወሰደቻቸው ቢያንስ ሁለት ጥበብ የተሞሉ እርምጃዎችን ተናገር።
4. ቁ23-25 ላይ የአቤጌል ዳዊትን አቀባበል ስንመለከት በምን መንገድ ነው ከባሏ ከናባል አቀባበል የሚለየው? ቁ26-28ትን በማንበብ በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ፤ ባሏ ያልተረዳውና ያልገባው ነገር ግን ይህች አስተዋይ ሴት የገባትና የተረዳችው ምን ነገር ትመለከታለህ?
5. ዳዊት በ1ኛ ሳሙ 24፡12 ላይ ከሳዖል ጋራ ባሳለፈው ሁኔታ ውስጥ በቀልን ይመለከት የነበረው በምን ሁኔታ ነበረ? 1ኛ ሳሙ 25፡26ና ቁ31ድን ስናነብ ዳዊት ራሱን ያገኘበት ሁኔታ በቀልን አስመልክቶ በልቡ ከሚያምነውና መመሪያው ጋራ ሲነጻጸር እንዴት ትመለከተዋለህ? አንተስ ልብህ የሚያምነው አንድ ነገር ሆኖ ስሜትህ ወደ ሌላ አቅጣጫ የመራህን ጊዜ ታስታውሳለህ ወይ?
6. ይህች ሴት ስለ ሳዖልና እንዲሁም ስለዳዊት መጨረሻ በትንቢት መልክ ቁ29 ላይ የምትናገራቸው ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር። ቁ29-35ትን ስንመለከት ይህች ሴት ዳዊት በዚህ አሁን በሚገኝበት ሁኔታ ውስጥ እንደማይቆይ እንደተረዳች መረዳት እንችላለን። ከነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የዳዊት መጨረሻ ዛሬ ከሚገኝበት ሁኔታ የተለየ እንደሚሆን የሚጠቁሙን ምን ዓይነት ተጨባጭ ሃሳቦችን ትመለከታለህ?
7. ቁ36-44ትን ስናነብ ይህች አቢጌል የተባለችውን ሴት በቁ3 ላይ የተነገረላትን ነገር እውነተኛነት የሚያረጋግጥ በተለይ አንድ ክፍል መርጠህ ተናገር። ምርጫህን ደግሞ ለምን እንደመረጥክ ምክንያትህን በመስጠት አስረዳ።
8. ቁ38ትን ስትመለከት እግዚአብሄር ለዳዊት ናባልን ሊበቀል ምን ያህል ጊዜ ነበረ የወሰደበት? አሳዳጁን ሳዖልንስ እግዚአብሄር እንዲበቀልለት ምን ያህል ጊዜ መጠበቅ ነበረበት? ከምቾታችን ይልቅ መለወጣችንን እንደሚፈልግ ይገባሃል ወይ? እግዚአብሄር በአንደኛ ደረጃ የሚገደው ምቾታችን ሳይሆን ክርስቶስን በእኛ ውስጥ ለመሳል በህይወታችን የሚሰራው ሥራ እንደሆነ ልንገነዘብ ያስፈልገናል።

# ጥናት ሃያ አምስት ፲ኛ ሳሙ 26፡1-25

የጥናት ዓላማ፡- በሳዖልና በሰራዊቱ ላይ እንቅልፍን በመጣል እግዚአብሄር ዳዊትን ያግዘው እንደነበረ፤ ዛሬም እኛ የተለያዩ ፈተናዎች ውስጥ ስናልፍ አምላካችን ከጎናችን ሆኖ የሚያደርግልንን ጥንቃቄ ማየት እንድንችል ዓይኖቻችንን መከፈት እንደሚኖርብን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "...ይህንን ያየም ሆነ ያወቀ ወይም የነቃ ማንም አልነበረም። ከእግዚአብሄር ዘንድ ከባድ እንቅልፍ ስለወደቀባቸው ሁሉም ተኝተው ነበርና። ፲ኛ ሳሙ 26፡12

1. ፲ኛ ሳሙ 26፡1-25 በአንድነት ይነበብ። ቁ1-4ትን ስናነብ "...ብለው ነገሩት። ስለዚህ ሳዖል ተነሳ" የሚል አነጋገርን እናነባለን። እነዚህ የዚፍ ሰዎች በሳዖልና በዳዊት ህይወት ውስጥ እየተጫወቱ ያሉት ሚና ምንድነው ብለህ ታስባለህ? ዳዊት ሳዖል እንደተከተለው ባወቀ ጊዜ ያደረገው ነገር ምን ነበረ? ዳዊት ይህንን ያደረገበት ምክንያት ለምን እንደሆነ ነው ከመንባቡ ውስጥ የምንረዳው?
2. ቁ4-6ትን ስናነብ ዳዊት ያሰበውን እቅድ ስራ ላይ ለማዋል ሶስት ደረጃዎችን ተከትሎ እንዳደረገ እንመለከታለን፤ እነዚህ ዳዊት የተከተላቸው ሶስት ደረጃዎች ምን ምን እንደነበሩ ተናገር። እነዚህን ቁጥሮች ስንመለከት ዳዊት ለእግዚአብሄር ነገር ያለውን ትክክለኛና ቅን የሆነ አመለካከት ለመማር እድል የነበራቸው ሁለት ሰዎች ማንና ማን ነበሩ?
3. የኢዮአብ ወንድም አቢሳ ዳዊት አብሮት እንዲሄድ የሰጠውን እድል በመጠቀም ከዳዊት ጋራ እንደሄደ ከቁ7 እንረዳለን። ቁ7-9ን ስንመለከት የዚህ ሰው ከዳዊት ጋራ መሄድ በዳዊት ህይወት ውስጥ በማያሻማ መንገድ ለሁለተኛ ጊዜ በሰውና በእግዚአብሄር ፊት እንዲረጋገጥለት የረዳው ነገር ምን ነበረ? አቢሳስ ከዳዊት ጋራ በመሄዱና ከእርሱ ጋራ ባሳለፈው ጊዜ ውስጥ ለራሱ ህይወት ሊጠቅመውና ሊረዳው የሚችል አንድ ሊማር የሚችለው ትልቅ የህይወት መመሪያ ምን ሊሆን ይችላል ብለህ ታምናለህ?
4. ቁ9-11ርን ስንመለከት ሳዖል በዳዊትም ሆነ በአቢሳ እጅ መገደል እንደሌለበት ምክንያት አድርጎ የተናገረው ነገር ምን ነበረ? በዳዊት አመለካከት ሳዖል እንዲሞት ካስፈለገ ሊሞት ስለሚችልባቸው አሟሟቶች ዳዊት የዘረዘራቸው ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር።
5. ቁ13-16 ላይ ስናነብ ዳዊት የሳዖልን የሰራዊት አለቃ አበኔርን ጠርቶ ሲያነጋግረው በመካከላቸው ሰፊ ርቀት እንደነበረ ይነግረናል። ለምን ይመስልሃል ዳዊት ይህንን ያህል ራቅ ማለት ያስፈለገው? ዳዊት በተደጋጋሚ ስለሳዖል በተናገረባቸው ወቅቶች ሁሉ በእግዚአብሄር እንደተቀባ አድርጎ ነው የሚያቀርበው፤ በዚህ ክፍል ውስጥ አበኔርን የሚወቅስበትና ሞት እንደሚገባው የሚነግረው ዋነኛው ምክንያት ምንድነው?
6. 17-20ን በማንበብ በተለይ ቁ19 ዳዊት የእርሱ አሳዳጅ አድርጎ የሚቆጥረው ማንን ነው? ይህንን ክፍል ስናነብ ዳዊት በስደት ከምድረበዳ ምድረበዳ ከመሳደዱ ሌላ ልቡ ከሚያዝንባቸው ነገሮች አንዱንና ዋነኛ የሆነውን ነገር በዚህ ቦታ ጠቅሶት እናገኘዋለን፤ ይህ የዳዊትን ልብ የሚያሳዝነው ነገር ምንድነው ትላለህ?
7. ቁ21-25ትን ስናይ ሳዖል ንስሃ ሲገባ እናነባለን፤ ዳዊት የሳዖል ንስሃ እውነተኛ እንደሆነና ከልቡ መሆኑን መጠራጠሩን የምናውቀው እንዴት ነው? ቁ24 ላይ ዳዊት የተናገረውን አነጋገር ስትመለከት፤ በኢየሱስ በሉቃ 6፡31 ላይ ከተናገረው አነጋገር ጋራ ያለው ተመሳሳይነት ምን እንደሆነ አስረዳ።
8. የዳዊትን ህይወት ለማጥፋት ሳዖል በሚያደገው ሙከራ ሁሉ ውስጥ፤ በበተለይም ቁ9-13ትን ስናነብ እግዚአብሄር ከዳዊት ጎን ተሰልፎ እየረዳው እንደሆነ የምናየው እንዴት ነው? በመከራ ውስጥ እየታሸህ ባለህበት ወቅት እግዚአብሄር ከጎንህ እንዳለ የተሰማህን ጊዜ ታስታውሳለህ ወይ? መከራን እየተጋፈጥን ባለንበት ወቅት እግዚአብሄር ከጎናችን ተሰልፎ እንዳለ ራሱን የሚያሳይባቸው የተለያዩ ሁኔታዎች ስላሉ ዓይኖቻችንን ከፍተን ልናይ ይገባናል።

# ጥናት ሃያ ስድስት ፲ኛ ሳሙ 27፡1-12

የጥናት ዓላማ፡- ከመከራው ክብደት በላይ አንዳንድ ጊዜ መከራው ከእኛ ጋራ የሚቆይበት የጊዜ ርዝመት ልብን ስለሚያዝል፤ እንደዳዊት ልባችንን ወይም ሥሜታችንን ከመስማት ይልቅ እግዚአብሄርን ለመስማት ጆሮዎቻችንን መክፈት እንደሚኖርብን ለመማር።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- “ዳዊት ግን በልቡ ከእነዚህ ቀናት በአንዱ በሳዖል እጅ መገደሌ ስለማይቀር የሚበጀኝ ወደ ፍልስጤማውያን ምድር መሸሽ ነው... ብሎ አሰበ።” 1ኛ ሳሙ 27፡1

1. 1ኛ ሳሙ 27፡1-12 በአንድነት ይነበብ። ቁ1 ላይ “ዳዊት ግን በልቡ...ብሎ አሰበ።” በማለት ይናገራል። ዳዊት በዚህን ጊዜ ሲነጋገር የሚገኘው ከማን ጋራ ነው? በዚህ ቁጥር ላይ ዳዊት አሁን ካለበት ሁኔታ ውስጥ ለመውጣት ሊጠቀምበት የወሰነው ነገር ምን እንደሆነ ተናገር። ስለ ዳዊት ህይወት ከምታውቀው በመነሳት፤ ዳዊት አንድን ነገር ለማድረግ ሲፈልግ በቅድሚያ የሚያማክረው ማንን ነው?
2. ዳዊት በቁ1 ላይ በልቡ ያሰበውና በቁ2 ላይ ደግሞ በተግባር ላይ ሲያውል የምንመለከተው ታክቲክ እንዳሰበው ሰርቶለታል ብለህ ታምናለህ ወይ? ዳዊት በእግዚአብሄር ህዝብ መሃል ሆኖ መከራን ከመቀበል ይልቅ በጠላት ምድር መኖር እንደሚበጀው እስከማመን ድረስ ያደረሰው ነገር ምንድነው ትላለህ? አንተስ ከምታልፍበት ሁኔታ የተነሳ ሥፍራህን ለቀህ ለመሄድና ሌላ እረፍት የሚሆንልህ ነገር ለመፈለግ ተፈትነህ ታውቃለህ ወይ?
3. ዳዊት በልቡ በማሰብ የወሰደው እርምጃ ከእርሱ ሌላ የህይወት አቅጣጫቸውን ያስቀየራቸውና እግዚአብሄር ከሰጣቸው ምድር ያፈናቀላቸው ምን ያህል ሰዎች ይታዩሃል? ቁ5ትን ስናነብ ዳዊት የፍልስጤምን ንጉስ አንኩስን አጠያየቁ ጊዜአዊ ማረፊያ ሥፍራ ነበረ ወይ የጠየቀው?
4. ቁ8-9ን ስንመለከት ዳዊት በፍልስጤም ሃገር መኖሪያ ተሰጥቶት ሲኖር እንዴት ይኖር እንደነበረ ይነግረናል። በዚህን ጊዜ ዳዊትና ከእርሱ ጋራ የነበሩት ሰዎች ኑሯቸውን የመሰረቱት በምን ላይ ነበረ? ንጉሱ አንኩስ በቁ10 ላይ ለሚጠይቀው ጥያቄ ዳዊት ይመልስ የነበረው መልስ ምን የሚል ነበረ? ይህ ዳዊት ለንጉሱ ይሰጥ የነበረው መልስ እውነትም ዳዊትና ሰዎቹ ያደርጉ የነበረውን ነገር የሚያንጸባርቅ ነበረ ወይ? አስረዳ።
5. ዳዊት ለንጉሱ ለአንኩስ የነገረውን ውሸት ለመደበቅ ሲል ይፈጽም የነበረው ሌላ ሃጥያት ምን ነበረ? ይህ በፍልስጤም ምድር የተለማመደው ነገር የአንድ ቀን ስህተት እንዳልሆነና በፍልስጤም ምድር እስከኖረበት ጊዜ ድረስ ቋሚ የህይወት ልምምዱ አድርጎት እንደኖረ ቁ11 ግልጽ አድርጎ ይነግረናል። ይህ በዚህ ምድር ላይ የተለማመደው ነገር በዳዊት ቀጣይ ህይወት ውስጥ ተግልጦ የሚታይበት ትዝ የሚልህ ሁኔታ ካለ ተናገር።
6. ዳዊት በምዕራፍ 26 ላይ የእግዚአብሄርን ስም ከአፉ ማውጣት እስከማይችል ድረስ ቢያንስ አስራ ሰባት ጊዜ ሲጠራው፤ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ግን አንድ ጊዜ እንኳን ለዓመል የአምላኩን ስም ሲጠራ አናይም። ይህ ዳዊት የገባበት ሁኔታ በዳዊት ላይ ለመፍረድ የሚያስቸግረን ቢሆንም እንኳን፤ ከዚህ ከዳዊት የህይወት ምዕራፍ ውስጥ ምን መማር የምንችለው ትምህርት አለ ትላለህ?
7. ዳዊት እግዚአብሄር ቀብቶት የህዝቡ መሪ እንደሚሆን የተናገረው ሰው በዚህ ዓይነት እግዚአብሄር በማይከብርበት ዓይነት ህይወት ለአንድ አመት ከአራት ወር ሙሉ ሲመላለስ እግዚአብሄር ዳዊትን በምህረት ማየቱ፤ በ1ኛ ሳሙ 26፡24 እና ሉቃስ 6፡31 ከምናነባቸው ሃሳቦች ጋራ በማነጻጸር ምን ተመሳሳይነት ይታይሃል?
8. ዳዊት የሚያልፍበት የመከራው ቀን መርዘሙ በህይወቱ ላይ ያስከተለው ምን ነገር ታያለህ? የምታልፍበት ነገር ጊዜው እየረዘመ ሲሄድ እግዚአብሄርን ሳይሆን የልብህን ስሜት የሰማህበት ጊዜ ታስታውሳለህ ወይ? ከመከራው ክብደት በላይ አንዳንድ ጊዜ የመከራው የጊዜ ርዝመት ልብን ስለሚያዝል፤ ከራስህ ጋራ መነጋገር ትተህ እግዚአብሄር የሚለውን ለመስማት ሞክር።

# ጥናት ሃያ ሰባት ፩ኛ ሳሙ 28፡1-25

የጥናት ዓላማ፡- በዳዊት ህይወት እንዳየነው ሁሉ ሳዖል በእግዚአብሄር ፍርሃት የተሞሉ አማካሪዎች ስላልነበሩት በቀላሉ ወደ ጥፋት እንደሄደ ሁሉ፤ እኛም አማካሪዎቻችን የእግዚአብሄር ፍርሃት የሞላባቸው ሰዎች ካልሆኑ እንደ ሳዖል ወደ ስህተት ለመሄድ ባሰብንበት ሰዓት ወደ ጥፋት ገፋፍተው ሊያስገቡን እንደሚችሉ ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ሳዖልም አገልጋዮቹን፤ እስቲ ሙታን ሳቢ ሴት ፈልጉልኝና ሄጄ ልጠይቃት አላቸው። እነርሱም ሙታን የምትስብ ሴት በዓይንዶር አለች አሉት።" ፩ኛ ሳሙ 28፡7  2ኛ ሳሙ 24፡1-3

1. ፩ኛ ሳሙ 28፡1-25 በአንድነት ይነበብ። አንኩስ የተባለው ሰው የጌት ንጉስ እንደነበረና የእስራኤልን አምላክ የተገዳደረው ጎልያድ ደግሞ ከዚሁ ከጌት እንደነበረ እናውቃለን። በቁ1 ላይ ዳዊት ምን ዓይነት ጥያቄ ሲቀርብለት ነው የምንመለከተው? የዳዊት መልስ ለንጉሱ ጥያቄ ምን የሚል ነበረ? ዳዊት ወደ ጠላት ምድር ሸሽቶ ራሱን ወጥመድ ውስጥ አስገብቷል ሊያሰኝ የሚችለው ወጥመድ ምን እንደሆነ ተናገር።
2. ቁ3 ላይ ስናነብ ሳዖል በእግዚአብሄር ፊት ደስ ትክክለኛ የሆነና እርሱን ሊያደስት የሚችል ያደረገው ነገር ምን ነበረ? ቁ7 ላይ ወርደን ስናነብ ደግሞ ሳዖል ቀድሞ የወሰደውን መልካም እርምጃ ወደራሱ ህይወት ዘልቆ ሲመጣበት ሥራ ላይ ለማዋል ሲቸገር እናየዋለን፤ ሳዖል ያወጣውና ራሱ ሊታዘዘው ሲቸገርበት የምታየው ህግ ምን ነበረ? ሳዖልን ወደዚህ የጣለውን ነገር ወደማንሳት ውስጥ እንዲገባ የገፋው ነገር ምን ነበረ? አንተስ ስትፈራና ስትጨነቅ ዓይንህን ወደማን ታነሳለህ?
3. ከቁ4-6 ያለውን ስናነብ ቁ5 ላይ "ሳዖል የፍልስጤማውያንን ሰራዊት ባየ ጊዜ ፈራ፤ ልቡም እግጅ ተሸበረ" የሚል ቃል እናነባለን። ፍልስጤማውያን ሰራዊታቸውን እንደሰበሰቡ ሁሉ ሳዖልም የራሱን ሰራዊት ሰብስቦ ነው የቀረበው፤ ታዲያ ሳዖልን እንዲህ ሊያስፈራውና ሊያስጨንቀው የቻልው ነገር ምን ነበረ? እነዚህን ሶስት ቁጥሮች ስታነብ ሳዖል ያደረገው አንድ ትክክለኛ ነገር ምንድነው ብለህ ታምናለህ?
4. በቁ6-7 ላይ ሳዖል እግዚአብሄርን ጠይቆ መልስ ሲያጣ ያደረገው ነገር ምንድነው?
5. በዚህች ሴት አነጋገር ቁ8-10ትን ስናነብ ሳዖል በሙታን ሳቢዎችና በመናፍስት ጠሪዎች ላይ ከዚህ በፊት ስለወሰዳቸው እርምጃዎች የምትናገራቸውን ነገሮች ዘርዝር። ሳዖል ራሱም ሆነ ወይም መናፍስት ጠሪዋ ሴት በማይታዘዙትና በማያከብሩት በእግዚአብሄር ሥም መማሉ ስለሳዖል ህይወት ምን ይነግርሃል?
6. ከቁ11-15 ያለውን ታሪክ ስታነብ በተለይ ቁ15 ላይ "እግዚአብሄር ከእኔ ርቋል" ብሎ ሲናገር እናነባለን። እውነት እግዚአብሄር ከእርሱ ርቋል ወይስ ሳዖል የተናገረውን የሚገልጥ የተሻለ ሃሳብ አለ ትላለህ? በቁ15 ላይ ደግሞ ሳዖል እግዚአብሄር እንዳልተናገረውና እንዳልመለሰለት ለሳሙኤል ይነግረዋል፤ በቁ16-19 ላይ በተለይም በቁ18 ሳሙኢል ሳዖልን ሊያስታውሰው የሚሞክረው አንድ ነገር ምንድነው? ይህንን መረዳቱ ምን ጥቅም ሊኖረው እንደሚችል አስረዳ።
7. ሳሙኤል ለተናገረው ንግግር የሳዖል ምላሽ ምን ነበረ? ሳዖል ይህንን ከሳሙኤል ጋራ ያደረገውን ውይይት ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ በዓይንዶር ያሳለፈውን ጊዜ ለራሱ ጠቃሚና ፍሬአማ አድርጎ ሊጠቀም የሚችልበት ምን መንገድ እንደሚታይህ ተናገር።
8. በቁ7 ላይ ሳዖል ወደ ስህተት መንገድ ለመሄድ ባሰበበት ሰዓት ያማከራቸው ወይም ሃሳቡን የገለጠላቸው ሰዎች በ2ኛ ሳሙ 24፡1-3 ዳዊት ወደ ስህተት መንገድ ለመሄድ ባሰበበት ሰዓት ባማከራቸው ሰዎች መሃል የምናየው ትልቅ ልዩነት  ምንድነው? አንተስ ሃሳብህን የምትገልጥላቸው ወይም የምታማክራቸው ሰዎች ምን ዓይነት ሰዎች ናቸው? ልናደርግ ያሰብነውን ውሳኔ የምናካፍላቸው ሰዎች እግዚአብሄርን የሚፈሩና እኛንም ከሃጥያት ለመታደግ የሚሞክሩ ሰዎች ሊሆኑ ይገባል።

# ጥናት ሃያ ስምንት ፲ኛ ሳሙ 29፡1-11

የጥናት ዓላማ፡- ዳዊት በንጉሱ ፊትና በግሉ ሁለት ዓይነት ህይወት ይኖር እንደነበረ፤ እኛም በቤተ ክርስትያን ከአማኞች ጋራ ስንሆን እንደ እግዚአብሄር መልዓክ የሚመስል ህይወትን ማሳየት፤ ከቤተ ክርስትያን ውጭ ደግሞ እንደ ሰይጣን መኖር በእግዚአብሄር ደስ የማይሰኝበት ዓይነት ህይወት እንደሆነ ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "በእኔ ዘንድ እንደ እግዚአብሄር መልዓክ መልካም እንደሆንህ አውቃለሁ።" ፲ኛ ሳሙ 29፡9

"እርሱ እንዲህ አድርጓል ብለው ይነግሩብናል ብሎ ስላሰበ ወንድም ሆነ ሴት በህይወት አስቀርቶ ወደ ጌት አላመጣም። በፍልስጤም ግዛት በኖረበት ዘመን ሁሉ እንዲህ ማድረጉ የተለመደ ነበረ። ፲ኛ ሳሙ 27፡11

1. ፲ኛ ሳሙ 29፡1-11 በአንድነት ይነበብ። ቁ1-3 ላይ ስናነብ ዳዊትና ከእርሱ ጋራ የነበሩት ሰዎች ራሳቸውን መጠየቅ የነበረባቸው፤ ነገር ግን የፍልስጤም አዛዦች የጠየቁት ጥያቄ ምን ነበረ? ይህንን ጥያቄ ዳዊትና ሰዎቹ ራሳቸውን ቢጠይቁ ምን ብለው መጠየቅ እንደነበረባቸው ተናገር።
2. በ፲ኛ ሳሙ 27፡10-12 ዳዊት በፍልስጤም ንጉስ ላይ ያደርገው የነበረውን ነገርና፤ በዛሬው ምንባብ ውስጥ ደግሞ ንጉሱ አንኩስ ስለዳዊት የነበረው አመለካከት ምን እንደሚመስል በማነጻጸር ተናገር። ዳዊት ዛሬ የሚገኝበትን የህይወት ሁኔታ እገባበታለሁ ብሎ ያላሰበው ነገር እንደማይሆን አያጠራጥርም፤ ታዲያ እኛ ከዚህ ነገር ምን መማር እንችላለን?
3. በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስናነብ ሳያል ከዳዊት ተሽሎ የተገኘበት አንድ ነገር ይታያል ብትባል ያ አንድ ነገር ምንድነው ትላለህ? ዳዊት ከፍልስጤማውያን ጋራ ሆኖ እስራኤልን ቢወጋ እግዚአብሄርን ይበድላል፤ ዞሮ ተመልሶ እስራኤልን በመርዳት ፍልስጤምን ቢወጋ ለንጉሱ በቁ8 ላይ የተናገረውን ነገር ቃል በመሻር እግዚአብሄርንና ሰዎችን ይበድላል። ከእነዚህ ሁለት ክፉ ምርጫዎች ውስጥ እንዳይገባ እግዚአብሄር ዳዊትን የከለለበት መንገድ ምን ነበረ?
4. ቁ4-5 ላይ ንጉሱ አንኩስና የሰራዊቱ አለቆች ስለዳዊት በሚያደርጉት ውይይት መሃል፤ ለዳዊት የቀድሞ ህይወቱንና ከእግዚአብሄር ህዝብ ጋራ የነበረውን ልምምድ ሊያስታውሰውና ወደ ልቡ ሊመልሰው የሚችል ምን አባባል ትመለከታለህ?
5. በቁ5-6 ላይ ስናነብ የፍልስጤም አለቆች የዳዊት ከእነርሱ ጋራ እስራኤልን ለመውጋት ለጦርነት መውጣቱ ለዳዊት ይከፍትለታል ብለው ያመኑት እድል ምንድነው? አንተስ እነዚህ የፍልስጤም አለቆች ያሰቡት ሃሳብ በእውነት ሊሰራለት ይችላል ብለህ ታምንበታለህ ወይ? ለምን ይህንን ማለት እንደቻልክ አስረዳ።
6. "ታዲያ ከንጉሱ ከጌታዬ ጠላቶች ጋራ የማልዋጋው ስለምንድነው?" በማለት በቁ8 ላይ ዳዊት ሲጠይቅ እንመለከታለን። ንጉሱ አንኩስ ምን በማለት ነው የሚመልስለት? በንጉሱና በፍልስጤም አዛዦች መሃል ዳዊትን አስመልክቶ ልዩነት እንዳለ እንረዳለን፤ በአንተ አመለካከት ንጉሱ ነው ወይስ አዛዦቹ ናቸው ትክክለኛ የሚመስሉህ? ተወያዩበት።
7. ቁ9 ላይ "በእኔ ዘንድ እንደ እግዚአብሄር መልዓክ መልካም እንደሆንህ አውቃለሁ።" በ፲ኛ ሳሙ 27፡11 ላይ ደግሞ የሚያደርገውን ነገሮች ንጉሱ እንዳይሰማ ዳዊት የሰዎችን ህይወት እስከማጥፋት እንደደረሰ እናነባለን። ዳዊት በአንድ በኩል እንደ መልአክ፤ በሌላ በኩል ደግሞ እንደ ሰይጣን በመኖር ማታለል የቻለው ማንን ነበረ? የማስመሰል ህይወት እግዚአብሄር ደስ የማይሰኝበት ዓይነት ስለሆነ ዘወትር በሰውም ሆነ በእግዚአብሄር ፊት አንድ ዓይነት ሰው ሆኖ መመላለስ ያስፈልጋል።

# ጥናት ሃያ ዘጠኝ ፩ኛ ሳሙ 30፡1-31

የጥናት ዓላማ፡- አለኝ የሚለውን ነገር ሁሉ ላጣው ለዳዊት የእግዚአብሄር ሥም ማረፊያ እንደሆነው ሁሉ፤ ወዳጅ ዘመድ፣ ሃብት ንብረትና የምንተማመንባቸው ጓደኞቻችን ሁሉ ከእኛ ጋራ ለመቆም የማይችሉበት ሰዓትና ጊዜ ሊመጣ እንደሚችል ተገንዝበን፤ በመከራ ጊዜ ሊያቆምና ሊያበረታን፣ ሃይል ሊሆነን የሚችለው በእግዚአብሄር ላይ ያለን እምነት ብቻ እንደሆነ ማወቅ እንዳለብን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ሰዎቹ ስለ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸው ነፍሳቸው ተመራ ሊወግሩት ስለተመካከሩ ዳዊት እጅግ ተጨነቀ፤ ነገር ግን ዳዊት በአምላኩ በእግዚአብሄር በረታ።" ፩ኛ ሳሙ 30፡6

1. ፩ኛ ሳሙ 30፡1-31 በአንድነት ይነበብ። እነዳዊት ከፍልስጤም ሰራዊት ጋራ ተሰልፈው እንዳይዋጉ ተከልክለው ወደየቤታቸው በተመለሱ ጊዜ የገጠማቸው ነገረ ምን ነበረ? በቁ1-3 ላይ ያለውን አንብበን መለስ ብለን ዳዊት በ፩ኛ ሳሙ 27፡8-10 ላይ ያደርግ የነበረውን ስናነብ እግዚአብሄር ለዳዊት በዚህም ሥፍራ እንደ ሥራው እንዳልከፈለውና ምህረት እንዳሳየው የሚጠቁመን ሃሳብ የትኛው ነው?
2. ቁ4-6 ላይ በከተማይቱ ላይና በራሳቸው ሚስቶችና ልጆች ላይ የሆነውን ነገር በተመለከቱ ጊዜ ዳዊትና ሰዎቹ ያደረጉት ነገር ምን ነበረ? ከእርሱ ጋራ ይወጡ ይገቡ የነበሩት የዳዊት ጓደኞች ዳዊትንም ጨምሮ ከፍተኛ ለቅሶ ካለቀሱ በኋላ የዳዊት ሰዎች ቀጥሎ እንደ መፍትሄ አድርገው በመውሰድ የፈለጉት እርምጃ ምን ነበረ? አንተስ እንደነዚህ ሰዎች ከችግር መውጫውን መፍትሄ ከመፈለግ ይልቅ በአካባቢህ ባሉት ሰዎች ላይ የተነሳህበት ጊዜ አለ ወይ?
3. ዳዊት ፍልስጤም ምድር ከገባበት ጊዜ ጀምሮ ከእግዚአብሄር ጋራ ምንም ዓይነት የቅርብ ግንኙነት ማድረግ ቀርቶ ስሙንም ሲያነሳ አናይም። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በተለይም ቁ7-8ትን ስታነብ፤ ዳዊት የእግዚአብሄርን ፊትና ፈቃዱን እንዲፈልግ ያደረገው ነገር ምንድነው ብለህ ታምናለህ? በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ምንም እንኳን ዳዊት ከአገሩ ከወጣ ጀምሮ በተለየ ሃጥያት ውስጥ ቢያልፍም እግዚአብሄር ጸሎቱን ሰምቶ ሲመልስለት እናያለን፤ በአንጻሩ በ፩ኛ ሳሙ 28፡15 ላይ ስንመለከት ግን ሳዖል እንዳልሰማው እናነባለን። እግዚአብሄር ሳዖልን ለመስማት እንቢ ብሎ ዳዊትን የሰማበት ምክንያት ምን ሊሆን እንደሚችል ሃሳብ ተለዋወጡ።
4. ቁ9-14 ላይ ዳዊትና ሰዎቹ በምድረበዳ ላይ ላገኙት ግብጻዊ ሰው ያደረጉትን የቸርነት እርምጃ እግዚአብሄር ለምን ሲጠቀምበት ነው የምንመለከተው? እነዳዊት በአጣዳፊ ተልዕኮ ላይ እንዳሉና ጊዜ ካጠፉ በምርኮ ለተወሰዱት ቤተሰቦቻቸው አደጋ እንደሚሆን እያወቁ ለምንድነው አንድ የእነርሱ ወገን ያልሆነን ሰው ለመርዳት ጊዜያቸውን የሚያጠፉት? አንተስ የራስህን በረከት ለመያዝ በምትቻኮልበት ወቅት በአካባቢህ የወደቁትና የአንተ ቸርነት የሚያስፈልጋቸውን አይንህን ከፍተህ ትመለከታለህ ወይ?
5. በቁ13 ላይ ዳዊት በጠየቀው ጥያቄና በቁ15 ላይ በጠየቀው ጥያቄ መሃል የሚታይህ ትልቅ ልዩነት ምንድነው? ዳዊት ይህንን ግብጻዊ ሰው ወራሪዎቹ ወዳሉበት እንዲያደርሰው ሲጠይቀው ሰውየው ዳዊት ቃል እንዲገባለት የጠየቃቸው ሁለት ነገሮች ምንና ምን ነበሩ? ቁ16-20ን ስናነብ ዳዊት በዚህ ሰው ምክንያት ማስመለስ የቻለው የምርኮ መጠን ምን ያህል እንደነበረ ተናገር።
6. በቁ21 እና በቁ22 ላይ የምናያቸው ሰዎች ከነዳዊት ጋራ ሆነው ጠላታቸውን ከማሳደድ ወደኋላ የቀሩበት ምክንያት ለምን ነበረ? ዳዊት ለነዚህ ሰዎች ባሳየው ሁኔታና አንዳንዶቹ የዳዊት ተከታዮች ባሳዩት ሁኔታ መሃል የምታየውን ልዩነት አስረዳ። እነዚህ ክፉዎችና ምናምንቴ ሰዎች ለደከሙት ወንድሞቻቸው የሰጡት ምላሽ በቁ23 ላይ ዳዊት ከተናገረው ንግግር ጋራ ስናይ የነዚህ ሰዎች ዋነኛ ችግርና መረዳት ያልቻሉት ነገር ምንድነው ብለህ ታምናለህ?
7. ቁ24-31 ላይ ስናነብ ከዚህ ሁኔታ በመነሳት ዳዊት ለእስራኤል ሁሉ ቋሚ ሥርዓት እንዲሆን ያደረገው ነገር ምን ነበረ? እነዚያ ከዳዊት ጋራ የነበሩት ክፉዎችና ምናምንቴ በመባል የተጠቀሱት ሰዎች የተንገበገቡለትን የምርኮ ንብረት ይግረማችሁ ብሎ ዳዊት ያደረገው ነገር ምን ታያለህ?
8. መለስ ብለን ቁ1-6ትን በትኩረት ስንመለከት ዳዊት ከህይወቱ ያጣቸው ወይም የተወሰዱበት ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ አንድ በአንድ ለመዘርዘር ሞክር። ዳዊት አለኝ የሚላቸው ሁሉ ከአጠገቡ ጠፍተው ባዶውን በቀረ ሰዓት ጉልበት የሆነውና ለመቆም የቻለው እንዴት ነበረ? አንተስ የተደገፍክበት ነገር ሁሉ ሲንሸራተት መደገፊያህ ማን ነው? የምንተማመንባቸው ነገሮች ከእኛ በተወሰዱ ጊዜ፤ ልንደገፍና ራሳችንን ልናሳርፍበት የምንችለው የማይለወጠው የእግዚአብሄር ሥም ብቻ እንደሆነ ልናውቅ ያስፈልገናል።

## ጥናት ሰላሳ 1ኛ ሳሙ 31፥1-13

የጥናት ዓላማ፡- ዳዊት ስለ ሳኦል ብዙ ሊናገር የሚችላቸው ክፉ ነገሮች እያሉ በመልካሙ ላይ ብቻ ማተኮር እንደወሰነ ሁሉ፤ እኛም በሰዎች ላይ የምናያቸው ክፉ ባህርያት ቢኖሩም እንኳን በእነርሱ ውስጥ ያለውን መልካም ነገር ብቻ ለማጉላት መወሰን እንደምንችል ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "እናንተ የእስራኤል ቆነጃጅት ሆይ ሃምራዊ ቀሚስና ቀጭን ፈትል ላለበሳችሁ፤ ልብሶቻችሁንም በወርቅ ዘቦ ላስጌጠላችሁ ለሳኦል አልቅሱለት።" 2ኛ ሳሙ 1፡24

1. 1ኛ ሳሙ 31፥1-13 በአንድነት ይነበብ። በቁ1 ላይ "በዚህ ጊዜ..." በማለት ጸሐፊው ጽሑፉን የጀመረው ስለየትኛው ጊዜ ሊጠቁመን ፈልጎ ነው?
2. በቁ3 ላይ የምናነበውን "ውግያው በሳኦል ላይ በረታበት ቀስተኞችም ደርሰው እጅግ አቆሰሉት። የሚለውን አነጋገር በማየትና፤ በቁ4 ላይ ደግሞ ሳኦል ከደረሰበት ሁኔታ በመነሳት የተናገረውን ንግግር ስንመለከት፤ ሳኦል የእግዚአብሄርን ቸርነት አድርጎለታል ሳኦል ግን አልተጠቀመበትም ማለት የምንችለው ለምንድነው?
3. ቁ4ትን ስንመለከት የሳኦል ዋነኛ ፍራቻው ምን እንደነበረ ነው የምናየው? አንተስ ሰዎች በሰዎች ፊት መናቅና መዋረድ ነው ወይስ ውርደትና ቅለትህ በእግዚአብሄር ፊት ቢሆን ነው ምርጫህ?
4. በ1ኛ ሳሙ 13፡13-14 ላይ እግዚአብሄር በሳኦል ህይወት የሚሆነውንና ያንንም ተከትሎ በዳዊት ህይወት አስመልክቶ በነብዩ ሳሙኤል ውስጥ የተናገረው ነገር በምዕ 31 ላይ ፍጻሜ ማግኘት ጀመረ ማለት የሚቻለው ለምንድነው? ይህ የእግዚአብሄር ቃል ለመፈጸም ቢያንስ ከ15-20 ዓመታት ፈጅቷል፤ ከዚህ ሁኔታ ውስጥ የተማርከው ነገር ምን እንደሆነ ለወገኖች አካፍል።
5. ቁ11-13 ላይ የኢያቢስ ገለዓድ ሰዎች ፍልስጤማውያን በሳኦል ላይ ያደረጉትን ነገር በሰሙ ጊዜ የወሰዱት እርምጃ ምን ነበረ? እነዚህ የኢያቢስ ገለዓድ ሰዎች ለሳኦልና ለልጆቹ ሲያደርጉ የምናየው ነገር ምን ያህል 1ኛ ሳሙ 11፥1-6 ላይ ሳኦል ካደረገላቸው ነገር ጋራ የተገኛኘ ነው ብላችሁ እንደምታምኑ ተወያዩበት። በማናቸውም ጊዜ ለእግዚአብሄር መንፈስ በመታዘዝ ለሰዎች የምናደርገውን ቸርነት እግዚአብሄር እንደማይረሳ ከዚህ መመልከት እንችላለን። ዕብ 6፡10
6. ሳኦል ባለመታዘዙ ምክንያት ሲሞት ራሱን ብቻ የጎዳ ሳይሆን በሌሎችም ህይወት ላይ ክፉ ነገርን አስከትሏል። በምዕራፍ 31 ውስጥ የምታያቸውን በሳኦል እግዚአብሄርን አለመታዘዝና በመሞቱ ምክንያት ተጎዱ የምትላቸውን ሰዎች እነማን እንደሆኑ ተናገር። እግዚአብሄር መልካሙን ዮናታንና ሌሎቹን ወንድሞቹን ከምድር እንዲወገዱ የፈቀደበት ምክንያት ለምን ይመስልሃል?
7. ሳኦልና ዳዊት አስቀድሞ የነበራቸውን ግንኙነትና ስላሳለፉት ሁኔታ ምንም አይነት እውቀት የሌለው ሰው፤ መዝሙረኛው በ2ኛ ሳሙ 1፡19-27 ላይ ለሳኦልና ለዮናታን ያወጣውን መዝሙር በማንበብ በዳዊትና በሳኦል መሃል ስላለው ግንኙነት ሊናገር የሚችለው ነገር ምን ይሆናል ብለህ ትገምታለህ?
8. ዳዊትን ለመግደል ሳኦል በተለያዩ ጊዜያት ጦር መወርወሩንና እየተከታተለ በገባ በወጣበት ሁሉ ያሳድደው እንደነበረ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ሆኖ እያለ ለምንድነው ዳዊት በ2ኛ ሳሙ 1፡19-27 የዘመረውን የፍቅር ዝማሬ ለማቅረብ የቻለው? አንተስ እጅግ በጣም አስቸጋሪ እንደሆነ ልብህ የሚያውቀውን ሰው መልካሙን ብቻ ለማሰብና ለመናገር ወስነህ ታውቃለህ? በእኛ ላይ ክፉ የሚሞኙ ብቻ ሳይሆኑ ክፉ ላደረጉብን ሰዎች ምላሻችን ፍቅር እንዲሆንና በቀሉን ለእግዚአብሄር መተው ማስተዋል ነው።